Wisdom at the source of the Blue Nile

እውነትን መፈለግና ስሌሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 4ኛ ዓመት፣ ቁጥር 7፣ ታህሳስ 2009

## ህትመት በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

**Expediting the completion of research projects and raising their quality**

Yinager Teklesellassie (PhD)

**The Untold Stories of College of Health Science**

Wendemagegn Enbiale (MD, MPH)

**The 70:30 Policy Dilemma: Resource Demands vis-à-vis the Policy**

*Kibrom Mengistu*

ለአዳዲስ ወላጆች /እናቶች/ ስለጨቅላ ህፃናት የእናት ጡት ማጥባት ጠቃሚ ምክር!

አማረ አለሙ

መፈንቅለ ስም (ወግ)

ደስታ ተከስተ





"አእምሮው በንባብ የበለፀገ ትውልድ በመፍጠር ሀገራችንን እናበልፅግ፡፡" በሚል መሪ ቃል በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ምክትል ፕሬዚደንት ጽ/ቤት፣ በአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም (አቋማተ) እና በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር - የባሕር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በትብብር የተዘጋጀ የ2009 ዓ. ም ዓመታዊ የንባብ ሳምንት እና የመጻሕፍት ዓውደ ርእይ ገጽታ በከፊል







"ለነገ ሃገር ተረካቢ ለሆኑ ህጻናት ምቹ፣ ለአካልና ለአእምሮ እድገታቸዉ ተስማሚ የሆነ፣ ከአደጋ የጸዳ የመዋያ አካባቢን ለመፍጠር ነዉ፡፡"

ሲስተር ኤደን አምሣለ

እውነትን መፈለግና ስሌሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

**Core Values**

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
አቶ አብይ መንክር
አቶ እምቢያለ በየነ
ወ/ሮ ሰውነት አለሙ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ቢሰማ ካሳ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
የኑስ ኑሬ

**ግራፊክስና ሌይአውት:-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች:-**
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች:-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ዛን ዌን (ዶ/ር)
ይናገር ተ/ስላሴ (ዶ/ር)
ወንድማገኝ እንቢያለ (ዶ/ር)
ክብሮም መንግስቱ
አማረ አለሙ
ደስታ ተከስተ
ታምሩ ከፈለኝ

**ፎቶ አንሺዎች:-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ:-**
የሻለም መንግስቴ
አለምነሽ

**ትራንስፖርት:-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች:-**
ይስሃቅ አቤልነህ
መልሸው አጥናፉ

ስልክ:- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# የንባብ ባህላችንን እንፈትሽ!

“ከአፍሪካውያን እይታ ልትደብቀው የምትፈልገውን ነገር መጽሐፍ ውስጥ አስቀምጠው” የሚል የፈረንጆች አባባል አለ:: ማንበብ በአፍሪካውያን ሕይወት ውስጥ ምንም ቦታ እንደሌለው ለማመልከት የሚናገሩት ነው፤ በአንድ አለም አቀፍ ጉባዔ ላይ የንባብ ባህልን አስመልክቶ በተጻፈ መልዕክት ግን ይህ አባባል ‘አፍሪካውያን እና ንባብ አይተዋወቁም’ ዓይነት ንቀት አዘል አስተያየት ሊሆን ይችላል የሚል ገለጻ ተሰጥቷል:: የእኛ የኢትዮጵያውያን የንባብ ባህልስ እንዴት ይገለጻል?

የንባብ ባህል ልክ እንደሌሎች ባህሎችና የማይዳሰሱ ቅርሶች ከትዉልድ ወደ ትውልድ በቅብብሎሽ የሚሄድ እና ሌሎች ባህሎችንም ለማስተላለፍ ሁነኛ መሳሪያ ሲሆን በዘመናችን የንባብ ባህል መጎልበት እንደስልጣኔ መለኪያ መዳከሙ ደግሞ የድንቁርና መነሻ ምልክት ተደርጎ መወሰድ ከጀመረ ሰነባብቷል:: አንዳንድ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች እንደሚሉት በኢትዮጵያ ቀደምት ስልጣኔ የድንጋይ ላይ ጽሁፎችና ቅርጻ ቅርጽን ጨምሮ በተለያዩ ዘመናት በጥቅም ላይ በዋሉ የአጻጻፍ ስልቶች በመጠቀም መልዕክትን ለማስተላለፍ በሚሞከርበት ዘመን ሰዎች ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ማለትም ለማንበብ የሚያስችል ክህሎት ለማግኘት ትምህርት እንደልብ ባልተስፋፋበት፣ ቢማሩም የሚነበበውን ነገር በቀላሉ ለማግኘት በማይቻልበት ዘመን ላይ ሆነው እንኳን የተሻለ የማንበብ ፍላጎትና ትጋት እንደነበራቸው ይነገራል::

በዘመናችን እውቀት እንደልብ በተስፋፋበት፣ የሚነበቡ ነገሮች እንደልብ በሚገኙበት ሁኔታ ውስጥ እያለን በተለይም ቋሚ እውቀት የሚያስጨብጡ የህትመት ውጤቶችን ለማንበብ የምናደርገው ጥረት አናሳ ሆኖ ይታያል:: በቀደመው ዘመን የህትመት ውጤቶች የሚነበቡት ከኢንተርኔት የሚገኙ የመረጃ ምንጮች ወይም ሌላ አማራጮች ባለመኖራቸው ነው ብለው የሚሞግቱ ቢኖሩም::

በታህሳስ ወር የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ምክትል ፕሬዚደንት ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ባሕር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና ከአማርኛ ቋንቋ ማበልጸጊያ ተቋም ጋር በመተባበር የንባብ ሳምንትና የመጻሕፍት ዓውደ ርእይ ማዘጋጀቱ ይታወሳል:: ይህ የንባብ ሳምንት በዋነኝነት የተዘጋጀው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲሁም የባሕር ዳር ከተማ ህብረተሰብ በተለይም ወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል የንባብ ፍቅር እንዲያድርበትና የንባብ ባህሉን እንዲያዳብር ንቅናቄ ለመፍጠርና ግንዛቤ ለማስጨበጥ አላማ አድርጎ ነው:: በንባብ ሳምንቱ ላይ የተገኘው ማህብረሰብ ግን ከተጠበቀው ቁጥር በጣም አነስተኛ ነበር:: የንባብ ባህላችን ምን ይመስላል? ለአንባቢው ቁጥር አነስተኛ መሆን ተጠያቂው ማነው? የንባብ ባህላችንን ለማሳደግ ምን መደረግ ይኖርበታል? አፋጣኝ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ሀገራዊ ጥያቄዎች ናቸው:: በዩኒቨርሲቲ ውስጥ መዘጋጀቱ የበለጠ አንባቢ ያገኛል ተብሎ ቢገመትም በትልቅ የትምህርት ተቋም ውስጥ ተካሂዶ በቂ አንባቢ ሳያገኝ መጠናቀቁ ደግሞ ተጨማሪ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ነው::

አሁን ላይ ያለው ወጣቱ ትውልድ ከሌላው ትውልድ የበለጠ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎችና ግኝቶች በጣም ቅርብ ነው:: ከየትኛውም ጊዜ ይልቅ አለም ወደ አንድ መንደር መምጣቷ ትውልዱ ማወቅ የሚፈልገውን እውቀትና መረጃ በፍጥነት ማግኘትና ማሰራጨት አስችሎታል:: ይህ እንደ ጥሩ አማራጭ ቢታይም ወደ ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ከቴክኖሎጂ ጋር ያለን የቅርብ ጊዜ ትውውቅና ለተፈለገበት መልካም አላማ ትውልዱ እየተጠቀመበት ነው ስንል ግን ጥያቄ ይጭርብናል:: ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ ጥናቶች መልስ ይስጡናል ብለን እንጠብቃለን:: ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎችና ግኝቶች በተጓዳኝ ግን የእውቀት መሰረታችን መጻሕፍቶቻችንና የንባብ ባህላችን ሊሆን ይገባል:: እነዚህ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራዎችና ግኝቶች ከንባብ የተገኙ መሆናቸውን መርሳት የለብንም::

ምንም እንኳን በሀገራችን የንባብ ባህል ዝቅተኛ መሆን የመጻሕፍት ዋጋ መናር እና የቤተ-መጻሕፍት ቁጥር አነስተኛ መሆን እንደ ዋና ችግር ቢጠቀሱም የንባብ ፍላጎት አለመኖር ግን ትልቁን ድርሻ ይይዛል:: ምሁራን እንደሚያስረዱት ህጻናትን ከመጻሕፍት ጋር በማገናኘት እና ከታች ጀምሮ በመኮትኮት የንባብ ባህላቸውን መለወጥ ይቻላል:: የንባብ ፍላጎትን ማሳደግ የቤተሰብ፣ የህብረተሰብ፣ የተቋማት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የመንግስት … ወዘተ የቤት ስራ ሊሆን ይገባል:: ስለ ሀገር እድገት ሲታሰብ ከቁሳዊ ልማት ባሻገር ሰብዓዊ ልማትም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: መጻሕፍት እና ንባብ በዚህ ረገድ ትልቁን ሚና እንደሚጫወቱ መግባባት ላይ መድረስ ያስፈልጋል::

ትውልዱ ራሱን ከሱሰኝነት፣ አልባሌ ቦታ ከመዋል፣ በአጓጉል ፊልሞች ከመናወዝ ተላቆ እንዲሁም የማንነታችን መለያ የሆኑ ሀገር-በቀል ዕውቀቶቻችን እና የታሪክ መረጃዎቻችንን ለማወቅና ለመረዳት ብሎም ለማጥናት ንባብ ትልቅ መሣሪያ መሆኑን መረዳት ይኖርበታል:: ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል አይደል የሚሉት አባቶቻችን! በእውቀትና በሥነ ምግባር የታነጸ ዜጋ ብሎም ማህበረሰብ ለማፍራት የንባብ ባህላችንን ለማሳደግ እንረባረብ!

## ቁልፍ መልዕክት

# ህትመት በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ከዩኒቨርሲቲያችን ተልዕኮዎች አንዱ ዕውቀትን ማዳበር እንደሆነ ይታወቃል:: በዚህም መሰረት ከመምህራን ስራዎች አንዱና ቁልፉ ስራ መመራመርና በዚህ ሂደት ያገኙትን አዲስ ዕውቀት በህትመት ለማህበረሰቡ ማዳረስን ያቅፋል:: በዚህ አጭር ጽሑፍ በራዕይ ጥበብ 2017 የህትመት አቅጣጫችንን በአጭሩ በማቅረብ በመምህራን ዘንድ ዋነኛ የመወያያ አርዕስት እንዲሆን በማድረግ ለራዕዩ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማስቻል ነው::

በራዕይ ጥበብ 2017 ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ይሆናል ሲባል ቢያንስ ሀምሳ (50) በመቶ የሚሆኑት መምህራን በአመት በትንሹ አንድ ህትመት በታወቁ የምርምር መጽሔቶች ላይ የሚያሳትሙ ይሆናሉ የሚለውን ግብ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ይታወቃል::

ባለፈው አመት የዩኒቨርሲቲው አስራ ስድስት (16) በመቶ የሚሆኑት መምህራን በአመት አንድና ከዚያ በላይ ማሳተም እንደቻሉ ያሳያል:: ከዚህ ካለንበት አፈፃፀም ተነስተን 2017 ዓ.ም ሀምሳ በመቶ የሚሆኑትን መምህራን በአመት ቢያንስ አንድ ህትመት የሚያሳትሙ ለማድረግ ግልጽ ስትራቴጂዎች ተቀምጠዋል:: መምህራንን በረጅም ስልጠና እንዲማሩ ማድረግና የተለያዩ የማሳተም አቅም የሚገነቡ ስልጠናዎችና ሰሚናሮች እንዲሳተፉ ማድረግንና በተፈጠሩት በርካታ ግንኙነቶች የመምህራንን ልማት ዋነኛ የትኩረት ነጥብ ማድረግ ስትራቴጂው ከሚያቅፋቸው ጉዳዮች ግንባር ቀደሞቹ ናቸው::

እነዚህ ስትራቴጂዎች እንዲሳኩ የመምህራን ንቁ ተሳትፎ ወሳኝ ነው:: ዩኒቨርሲቲው የማያሳትም ወይም የማታሳትም መምህር/ት እንደዩኒቨርሲቲ መምህር/ት አይቆጠርም/ አትቆጠርም የሚባለው እና በሌሎች በአደጉ ዩኒቨርሲቲዎች የሚተገበረው publish or perish መርህ በቅርቡ መተግበሩ አይቀሬ መሆኑን በመረዳት መምህራን ለምርምር የተለየ ትኩረት መስጠት ይገባቸዋል:: የዩኒቨርሲቲው ሁሉም አመራሮች ለሚያሳትሙ መምህራን ልዩ ከበሬታና ድጋፍ በመስጠት እንዲበረታቱና ለዩኒቨርሲቲው ዋነኛ መገለጫ መሆናቸውን ሁሌም ማስታወስ ተገቢ ነው::

በአሁኑ ወቅት የማናሳትም መምህራን በጊዜያዊነት ለአቅም ግንባታ የተሰጠንን ጊዜ ሳናባክን በፍጥነት ወደ ማሳተም ልንሸጋገር ይገባል:: ዕውቀትን የማይተነትንና ውስንነቶችን የማይለይ እና የማይሞላ አቅም ለማስተማርም አይበጅም:: በምርምር ዩኒቨርሲቲ የጥሩ አስተማሪነት መሰረት ጥሩ ተመራማሪነት ነው:: ያለምርምር ማስተማር በዩኒቨርሲቲ ሊታሰብ አይችልም:: በመሆኑም ሁላችንም ተመራማሪ መምህራን ለመፍጠር እንረባረብ::

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

## የአዘጋጁ መልዕክት

ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

በዚህ በያዝነው ወር ማህበረሰቡ የንባብ ፍቅር እንዲያድርበትና የንባብ ባህሉን እንዲያዳብር ንቅናቄ ለመፍጠርና ግንዛቤ ለማስጨበጥ አላማ ያለው በዩኒቨርሲቲያችን የንባብ ሳምንት ተዘጋጅቶ ነበር:: የተማረ ሰው መፍለቂያ እና ሀገር ወዳድ ዜጋ ለመፍጠር ቀና ደፋ ከሚለው ዩኒቨርሲቲ የተሳተፈው ማህበረሰብ ግን እጅግ በጣም አነስተኛ ነበር:: የንባብ ባህላችን ምን ይመስላል? የተሳታፊው ቁጥር አነስተኛ መሆን ተጠያቂው ማነው? የንባብ ባህላችንን ለማሳደግ ምን መደረግ ይኖርበታል? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያላችሁን ሃሳብና አስተያየት ለመቀበል ናይል ጋዜጣ እንሆ ትላለች:: እንወያይበት፣ እንከራከርበት እና የጋራ መፍትሄ እናምጣ ትላለች ናይል!

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

# አበይት ዜናዎች

## በግንባታው ዘርፍ ያሉ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ተገለጸ

በታድዬ አስማረ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አዘጋጅነት የግንባታው ዘርፍ የበለጠ ለማሳደግና ለማዘመን በሚል አላማ የሁለት ቀን አውደ ጥናት ተካሄደ፡፡

አውደ ጥናቱን የከፈቱት የኢፌድሪ ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስተር ዶ/ር አምባቸው መኮንን ኢትዮጵያ በግንባታው ዘርፍ ከፍተኛ እምርታ እያሳየች መሆኑን ገልጸው በተለይም በመንገድ፣ በባቡር፣ በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በውሃ አቅርቦትና በመስኖ ሥራዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ረገድ ከፍተኛ ሥራዎች መሰራታቸውን ተናግረዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩት አካላት አቅም ማነስ እና በብልሹ አሰራር ችግር ምክንያት ግን ዘርፉ የበለጠ እንዳያድግ እያደረገው መሆኑን የጠቆሙት ዶ/ር አምባቸው ዘርፉ የበለጠ እንዲያድግ ካስፈለገ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት የሙያ ስነምግባርን በማክበር፣ በቅንነትና በታማኝነት በመስራት እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ለዘርፉ የበለጠ እድገት እና ዘመናዊነት በቅንጅት መሥራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የውሃና ሲቪል ምህንድስና ዲን ዶ/ር ወንድሙ ተመስገን በበኩላቸው የግንባታውን ዘርፍ የበለጠ በማሳደግ ረገድ ዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር በመክፈት በርካታ ምርምሮች እንዲሰሩ በማድረግ እና የማማከር ሥራ በመስራት ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል፡፡

የአውደ ጥናቱ አላማ በግንባታ ዘርፉ ባለድርሻ አካላት በአንድ መድረክ በማገናኘት አሁን በዘርፉ እየታዩ ያሉ ችግሮች ላይ በመወያየት መፍትሄ ለማበጀት እና ስምምነት ለመፍጠር መሆኑን የኢንስቲትዩቱ ሳይንቲፊክ ዳይሬክተር ዶ/ር ንጉስ ጋብዬ ገልጸውልናል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ላይ በመሆኑ በአውደ ጥናቱ ተለይተው የተቀመጡ ችግሮች ላይ በማተኮር የዩኒቨርሲቲውን ድርሻ በመውሰድ የስርአተ ትምህርት እስከ ማሻሻል ድረስ በመሄድ ዘርፉ የሚፈልገውን ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማሰልጠን አውደ ጥናቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ምሁራን፣ ከኮንስትራክሽን እና ከአማካሪ ድርጅቶች የመጡ ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች ከነመፍትሄያቸው የሚያመለክቱ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው የመፍትሄ አቅጣጫዎችንም በማስቀመጥ ተጠናቋል፡፡

## ቤተ-መዘክሩን ለማደራጀት የምክክር ውይይት ተካሄደ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮምኒኬሽን ጽ/ቤት አዘጋጅነት የዩኒቨርሲቲውን ቤተ-መዘክር ለማደራጀት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በዩኒቨርሲቲው የሴኔት አዳራሽ የምክክር መድረክ ተካሄደ፡፡

የጽ/ቤቱ ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ጥሪውን አክብረው ለመጡ ታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው ቤተ-መዘክሩን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮምኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት በመሆኑ እና አሁን በተጨባጭ ያለበት ደረጃ ዝቅተኛ በመሆኑ በአገር አቀፍ ደረጃ ማሟላት የሚገባውን አሟልቶ ቤተ-መዘክሩን በተጠናከረ መልኩ ለማደራጀት የውይይት መድረኩ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው አስገንዝበዋል፡፡ ቤተ-መዘክሩ ታሪክን ለማስተዳደር እና ለመመርመር፣ ቅርስን ለመጠበቅ እንዲሁም ለሀገሪቱ ብሎም ለዩኒቨርሲቲው ጎብኝዎች ምቹ ቦታ ለመፍጠርና ለምርምር አመቺ ለማድረግ ያለው ጠቀሜታ በርካታ በመሆኑ የምክክር መድረኩ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ከውጭ ለመጡ ባለድርሻ አካላት የማንቂያ ደወል መሆኑን ዶ/ር ፍቅረሰላም ገልጸዋል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የዩኒቨርሲቲው የታሪክ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ በሆኑት በአቶ ታረቀኝ አለሙ የቤተ-መዘክር ፅንሰ-ሀሳብ ምን እንደሚመስል የሚያወሳ ፅሁፍ ቀርቦ የመወያያ ነጥቦችን በመለየት ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ ቤተ-መዘክሩ ገና በጅምር ላይ ቢሆንም ያሉት ችግሮች በታዳሚዎች ተጠቁመው የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች፣ የፎክሎር እና የሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍሎች መምህራን እና ተማሪዎች፣ የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ተማሪዎች እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በምክክር መድረኩ ላይ የተሳተፉ ሲሆን ቤተ-መዘክር መረጃንና መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ቅርስን ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ ከማስተላለፉ ባሻገር ለምርምሩም የመረጃ ቋት ሆኖ እንደሚያገለግል ገልጸው ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክትና ለወደፊት ቤተ-መዘክሩ ደረጃውን ጠብቆ መደራጀት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

To follow the latest news about BDU, check out our website:

**www.bdu.edu.et**

facebook page:

**www.facebook.com/bduethiopia**

## ኮሌጁ የቱሪዝም ሣምንትን አከበረ

ሙሉጐጃም አንዱአለም

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የቱሪዝምና ሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል አዘጋጅነት ሦስተኛውን ዓመታዊ የማይስ (MICE) ቱሪዝም ሣምንት "ቱሪዝም ለአካባቢ ኢኮኖሚ ያለው ፋይዳ በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ተከበረ፡፡

የዝግጅቱ አካል የሆነውን ህዝበ ገለጻ በንግግር የከፈቱት የኮሌጁ ዲን አቶ በላይነው አስሬ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር እንደቆየና ከዚሁ ጋር ተዛማጅ የሆነ ጥናታዊ ፅሑፍ ቀርቦ የውይይት መድረክ መፈጠሩ ስለ ቱሪዝም፣ ባህልና ቅርስ አጠባበቅ ግንዛቤ ለመፍጠር ፣ የባህል ልውውጥ ለማድረግ እንዲሁም በዘርፉ ለአሰራር የማይመቹና መቀረፍ ያለባቸው ችግሮች እንደዲቀረፉ ለማስቻል ጉልህ ድርሻ እንዳለው ገልጸው ዩኒቨርስቲው ከክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋር የተቀናጀ ስራ ለመስራት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ዩኒቨርሲቲው ብሎም ኮሌጁ ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ቱሪስት ከጎበኛቸው አገሮች መካከል በ12ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ፣ በሀገሪቱ ብሎም በክልሉ ያለውን የባህልና ቱሪዝም ነባራዊ ሁኔታ እና የባህል እንክብካቤ ልማድን እንዴት ማዳበር እንዳለብን ከክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከመጡት ከአቶ ልኡል ዩሐንስ ጥናታዊ ጽሑፍ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የዝግጅቱ ታዳሚዎች የኮሌጁ አመራሮች፣ መምህራን፣ የት/ክፍሉ ተማሪዎች እንዲሁም ከግልና ከመንግስት ተቋማት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተገኙ ሲሆን ከውይይቱ በርካታ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ገልፀዋል፡፡ በፅንሰ ሀሳብ የተገለፀው ወደ ተግባር ተቀይሮ በርካታ አኩሪ ተግባራት መሥራት የሚቻልበት መንገድ በቅርቡ እንዲመቻች ከዩኒቨርሲቲው ውጭ የመጡ ተጋባዥና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አሳስበዋል፡፡

የግቢ ፅዳት፣ አውደ ርዕይ፣ የተማሪዎች የስዕል፣ የጠቅላላ እዉቀትና የስነ ፅሑፍ ውድድር የተካሄደ ሲሆን ለአሸናፊዎች የሜዳሊያ ሽልማትና የምስክር ወረቀት እንዲሁም ለበአሉ መሣካት ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱት ተቋማት የምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ የስራ ፈጠራ ማዕከል ለማቋቋም የምክክር መድረክ አዘጋጀ

በሙሉጐጃም አንዱአለም


የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የቴክኖሎጂ የስራ ፈጠራ ማዕከል ለማቋቋም ከGIZ-STEP ድርጅት በመጡና በሙያው ጥልቅ ዕውቀት ባላቸው ምሁራን ውይይት ተካሂዷል፡፡

የውይይቱ ዋና ዓላማ በሥራ ፈጠራ (Business incubator) ዙሪያ በሙያው ያካበተ ልምድ ካላቸው ምሁራን ጋር እና ከተለያዩ ተቋማት የሚነሱ ሀሳቦችን አሰባስቦ በኢንስቲትዩቱ ሊቋቋም የታሰበው ማዕከል አስፈላጊነት እና አጋር ድርጅቶችን ለይቶ ለማውጣት ታልሞ እንደሆነ የኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪ ትስስርና የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶ/ር ሲሳይ ገረመው ገልፀዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራሮች፣ መምህራን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የውይይቱ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ከGIZ-STEP ተቋም በመጡ ባለሙያዎች የቀረበው ፅሁፍ የሥራ ፈጠራን የመነሻ ፅንሰ ሀሳብ የሚያወሳ በመሆኑ በቀረበው የመነሻ ሀሳብ ላይ በመወያየት ማዕከሉ ቢቋቋም አብሮ ለመስራት ፈቃደኛ መሆናቸውንና ከቀረበው ገለፃ ግንዛቤ መጨበጣቸውን ተናግረዋል፡፡

# ለአዳዲስ ወላጆች /እናቶች/ ስለጨቅላ ህፃናት የእናት ጡት ማጥባት ጠቃሚ ምክር!

በአማረ አለሙ
በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሚድዋይፈሪ ት/ክፍል መምህር
ኢሜል፡ ame439@yahoo.com



ጡት ማጥባት በተፈጥሮ የተሰጠ የእናትነት ጸጋ ነው:: ይሁንና አንዳንድ እናቶች ይህንን ስጦታ በአግባቡ ሲጠቀሙበት አይታዩም:: በመሆኑም ስጦታቸውን በሚገባ ለመጠቀም ሁሉም እናቶች እራሳቸውን በአዕምሮ ዝግጁ ማድረግ ይገባቸዋል:: ስለጡት ማጥባት ጥቅምም ሰፊ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይገባል:: ከዚያ ባለፈ ደግሞ ጡት የሚያጠቡ እናቶች እራሳቸውን መንከባከብ፣ ፈሳሽ ነገሮችን መውሰድና ምግብን የተመጣጠነ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: በቂ እረፍት ማድረግም እንዲሁ:: ታዲያ ይህንን እንዲያደርጉ ማን ምን ማድረግ አለበት? ከማንስ ምን ይጠበቃል? የሚለውን ጥያቄ ምላሽ ሰጪው ሁሉም ማህበረሰብ መሆን አለበት::

የእናት ጡት ወተት ከምግብነቱ ባሻገር፣ በእናትና ልጅ መካከል ያለውን መስተጋብር /ትስስር (bonding) ያጠነክራል:: ለዚህም በቤተሰብ ውስጥ ፍቅር እንዲኖር ያግዛል:: እናቲቱ በጡት ካንሰር (breast cancer) በሽታ እንዳትያዝ እና ለማህፀን ካንሰር (cervical cancer) ተጋላጭ እንዳትሆን ይረዳታል:: በእርግዝና ምክንያት የሚመጣውን የሰውነት ክብደትና የደም መፍሰስ መጠንም ይቀንስላታል:: የእንግዴ ልጁም ቢሆን ቶሎ እንዲወርድ፣ ማህጸኗ ወደ ነበረበት ቦታ እንዲመለስም ያደርጋል:: እንደ ወሊድ መከላከያነትም (birth control) ያገለግላታል::

ጡት ማጥባት የሰውነት ቅርጽን በመጠበቅ የጎላ ሚና አለው:: ይሁንና አንዳንድ ወላጆች ግን ይህንን ሀሳብ አይቀበሉትም:: ይልቁንም "ጡት የማጥቢያ ጊዜዬን ለጂም መጠቀም ይኖርብኛል፤ ምክንያቱም ከወለድሁ በኋላ ቅርጼ የተበላሸ ስለሚሆን መስተካከል አለበት:: ጡት ከማጠባ የታሸገ ወተትና መሰል የእናት ጡት ወተትን ሊተካ የሚችል ንጥረ ነገር ለልጄ መስጠት አለብኝ" ብለው ያምናሉ:: ይህ ግን ፈፅሞ ትክክል አይደለም:: ለአብነትም በመጀመሪያዎቹ ቀናት የልጁ የጨጓራ መጠን እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ከእናት ጡት የሚወጣው የመጀመሪያ ቢጫ ወተት (እንገር (colostrum)) ለሕፃኑ በበቂ ሁኔታ ተመጥኖ ይመረታል:: ስለዚህም ይህንን ልኬታ በመተው ሕፃኑ የቆርቆሮ ወተት እንዲወስድ ቢደረግ ወይም የእናት ጡት ወተት ባይጠባ በተለያዩ በሽታዎች ይያዛል /ይጋለጣል/::

በእርግጥ በአንዳንድ ምክንያቶች ልጆቻቸውን ማጥባት የማይችሉ እናቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ለአብነትም የአዕምሮ ህሙማን፤ እናቲቱ በጤና እክል ምክንያት የጤና ባለሙያው ከከለከላትና የልጁ ሁኔታ እንዳይጠባ የሚከለክል ከሆነ እናቲቱ ጡት ላታጠባ ትችላለች፤ ማለትም ልጁ እድሜውን ሳይጨርስ ይወለድና (pre-term birth) የመጥባት አቅሙ አናሳ ይሆናል:: በዚህም ሳቢያ የእናቱ ጡት ወተት ታልቦ በጤና ባለሙያ እርዳታ እንዲጠባ ይደረጋል::

አንዳንድ ጊዜ በዘልማድ አንዲት እናት በኤች አይቪ /ኤድስ (HIV/ AIDS) ከተያዘች ልጇን ጡት ማጥባት የለባትም የሚሉ አሉ:: እንደ ጤና ባለሙያ ይህ አባባል ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም ህመምተኛዋ ወላጅ እናት፣ ከመውለዷም በፊት ሆነ ከወለደች በኋላ ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚግዝ PMTCT (Prevention of Mother-to-Child Transmission)) የህክምና እርዳታ ይደረግላታል:: ከዚያ ባለፈ ደግሞ እናቲቱም ሆነ ልጁ የሚወስዱት መድኃኒት ስላለ በሽታው ወደ ሕጻኑ ሙሉ በሙሉ የመተላለፍ ኃይል አይኖረውም::

በአሁኑ ወቅት እናቶች ልጆቻቸውን ጡት ከማጥባት ይልቅ ከእራሳቸው ጡት አስበልጠው በሚተዋወቁ የቆርቆሮ ወተቶች ልጆቻቸውን ሲመግቡ ማየት የተለመደ ተግባር ሆኗል:: በተለይ በከተማ የሚኖሩና ሠራተኛ ሴቶች ትኩረት የሚሰጡት በቆርቆሮ ወተቶች ላይ ነው:: ይሁንና የእናት ጡት ወተትን የሚተካ ምንም ነገር እንደሌለ መረጃዎች ያሳያሉ:: በመሆኑም እናቶች ጡት በማጥባት እራሳቸውንም ሆነ ልጃቸውን ከተለያየ በሽታ መታደግ ይኖርባቸዋል::

በእርግጥ ይህንን የቆርቆሮ ወተት እንደ ተጨማሪ ምግብነት መጠቀም ይቻላል:: ይሁንና መጠቀም ያለባቸው ስድስት ወር ልጃቸውን ጡት ብቻ ካጠቡ በኋላ ወይም ልጃቸው በጣም እንዲጠነክርና ብሩህ አዕምሮ ያለው እንዲሆን ከፈለጉ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ የእናት ጡት ካጠቡ በኋላ ቢሆን ይመከራል::

የእናት ጡት ወተት ለሕጻናቱም ቢሆን ከተለያዩ ኢንፌክሽን አምጪ ተህዋስያን ለምሳሌ:- ከተቅማጥ፣ ከሳንባ፣ ከጆሮና ከሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ይከላከላል:: በአስምና አለርጂ ህመም እንዳይያዙ፣ ለአጥንት ጥንካሬና እድገት፣ ለአዕምሮ እድገትም ጠቃሚ ነው:: በአፍ ውስጥ ለሚገኙ ጡንቻዎች ጥንካሬና ለፊት ጡንቻዎች እድገትም ወሳኝ ነው:: ጤናማ ዓይን እንዲኖራቸውና የሆድ ድርቀት እንዳይከሰትባቸው፤ በሽታ የመከላከል አቅም እንዲኖራቸውም ያግዛቸዋልም:: ለቤተሰብም ቢሆን ካለ አግባብ የሚያወጡትን ወጪ ይቀንስላቸዋል:: ለአብነትም የወተት፣ የህክምናና መሰል ወጪዎችን እንዳያወጡ ያደርጋል::

> "ልጅን እስከ ስድስት ወር የእናት ጡት ብቻ ሳያጠቡ ሌሎች ነገሮችን መቀላቀል ልጁን ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጋለጥ ማድረግ ነው::"

የጡት ወተትን ልጁ በተወለደ ግማሽ ሰዓት ውስጥ ማጥባት ይገባል:: በተለይም የመጀመሪያውን ቢጫ ወተት - እንገር (colostrum)) ልጁ የሚያገኘ ከሆነ በሽታን የሚከላከሉ ንጥረ ነገሮችን ስለሚይዝ ለልጁ እንደ መጀመሪያ ክትባት (Immunization/Vaccination) ያገለግለዋል:: በመሆኑም ይህንን ወተት መመገብ እናቶች የሁልጊዜ ሥራቸው ሊያደርጉት ይገባል::

እናቶች በባህሪያቸው ብዙ ጊዜ ለልጆቻቸው ይሳሳሉ:: ከዚህም የተነሳ "ጡቴ በቂ ወተት የለውም" በማለት ሌሎች ምግቦችን ወይም ከጡት ወተት ውጪ የሆኑ ወተቶችን ይመግባሉ:: ይህ ደግሞ ሕጻኑ ከእናት ጡት ወተት ሊያገኘው የሚችለውን ጥቅም ያሳጣዋል:: ማንኛዋም እናት እንደ ወለደችው ልጅ መጠን ማለትም መንታና ከዚያ በላይ እንኳን ቢሆን በዚያው ልክ ወተት የማምረት አቅም አላት:: ስለዚህም በቂ ወተት የለኝም ማለት አይቻልም:: በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ወተቱ አነስተኛ ሊሆን ይችላል:: ይሁንና ልጇን ቶሎ ቶሎ በማጥባት የወተት መጠኑ እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል::

የእናት ጡት ወተትን አንድ ሕፃን ልጅ ቢያንስ በቀን ከስምንት እስከ አስራ ሁለት ጊዜ ማግኘት ይኖርበታል:: "ልጅን እስከ ስድስት ወር የእናት ጡት ብቻ ሳያጠቡ ሌሎች ነገሮችን መቀላቀል ልጁን ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጋለጥ ማድረግ ነው::" ሕጻኑ በቂ ወተት እንዳገኘ እናቲቱ ለመረዳት ስትፈልግ የተለያዩ ምልክቶች ልታይ ትችላለች:: ከእነዚህም መካከል ሽንቱን በቀን ከስድስት ጊዜ በላይ ይሸናል፤ ኪሎውም በተከታታይነት ከፍ እያለ ይሄዳል::

በአጠቃላይ ስለ እናት ጡት ወተት ጠቀሜታ ማህበረሰቡ ሰፊ ግንዛቤ እንዲይዝ በማድረግ ተግባሩ ላይ ሁሉም የድርሻውን መወጣት አለበት:: አንድ ጊዜ የታለበውን የጡት ወተት ከስድስት እስከ ስምንት ሰዓት ቀዝቀዝ ባለ ቦታ ከተቀመጠ፤ ፍሪጅ ውስጥ ደግሞ በረዶ ክፍል ሳይገባ 72 ሰዓት፤ በረዶ ክፍል ከገባ ሦስት ወር ድረስ አቆይተው መመገብ ይችላሉና እናቶች በቀላሉ የተፈጥሮ ጸጋቸውን ያለምንም ክፍያ ለልጃቸው ማካፈል ይችላሉ::

የእናት ጡት ወተት ዋጋ ከፍተኛ ነው፤ እናቶች ለህፃን ልጆቻቸው በሚለግሱት የጡት ወተት ጤናው የተጠበቀ ትውልድ ማፍራት ይቻላል::
"የእናት ጡት ወተት ለሕጻናት"::

ስለ እናት ጡት ወተት ማጥባት ጠቃሚ ምክሮች:-
ጨቅላ ህፃንዎን ጡት ማጥባት ያለማቋረጥ የሚደረግ ሃላፊነት ነዉ:: አዲስ ከተወለደው ልጅዎ ጋር የጠበቀ ግንኙነት (bonding) ለመመስረት ጥሩ አጋጣሚንም ይፈጥርልዎታል:: ስለሆነም የሚከተሉት ሰባት ነጥቦች /ምክሮች/ ጨቅላ ህፃንዎን ጡት ለማጥባት ይረዳዎታል::

1ኛ. <u>የጡት ወተት ብቻ ይጠቀሙ (Give Only Breast Milk)</u> :-
ብዙዉን ጊዜ ለህፃናት እድገት የሚመከረዉና የሚመረጠዉ የእናት ጡት ወተት ብቻ ነዉ:: ጡትዎን እንዳያጠቡ የሚያስገድድዎ ነገር ካለ /ጡት ማጥባት የማይችሉ ከሆነ/ ግን የቆርቆሮ ወተቶችን (ፎርሙላ ወተትን) መጠቀም ይቻላል:: ጤናማ ህፃናት እስከ 6 ወር ድረስ ዉሃ፣ ጭማቂም ይሁን ሌላ ፈሳሾችም ቢሆን አያስፈልጋቸዉም:: (ጡትና ጡት ብቻ መጥባት አለባቸው::)

2ኛ. <u>አዲስ የተወለደ ልጅዎን በበቂ ሁኔታ ያጥቡት (Optimal Breast Feeding)</u>:-
አዲስ የተወለደ ልጅዎ በቀን ከስምንት እስከ አስራ ሁለት ጊዜ ጡት መጥባት ይገባዋል:: ይህ ማለት በየሁለትና ሶስት ሰዓት ልዩነት ማጥባት ያስፈልጋል ማለት ነዉ:: ህፃኑ ጡት ሲፈልግ /ሲራብ የመወራጨት፣ የመጥባት ምልክቶችንና ከንፈሮቹን ማንቀሳቀስ ይጀምራል:: እነዚህን አይተዉ ካላጠቡት ማልቀስ ይጀምራል:: ልጅዎ መጥባቱን ካቆመ ወይም አፉን ከዘጋ አልያም ፊቱን ከጡት ላይ ካዞረ የመጥገብ ምልክት ሊሆን ይችላል ወይም እረፍት እየወሰደ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም ጡትዎን ከመስጠትዎ በፊት ትንሽ ጊዜ ይጠብቁት:: የልጅዎ እድሜ እየጨመረ ሲመጣ በትንሽ ሰዓት ዉስጥ ብዙ እየጠባ ይመጣል::

3ኛ. <u>ቫይታሚን ዲ ይስጡት (Provide Supplement Vitamin D)</u> :-
የጡት ወተት ለልጅዎ አጥንት ጥንካሬ የሚሰጡ እንደ ካልሲየምና ፎስፈረስ ያሉ ማዕድናቶች ከልጅዎ አንጀት እንዲመጠጥ የሚያደረገዉን ቫይታሚን ዲ (Vit D) በበቂ መጠን ስለሌለዉ የጤና ባለሙያዎን በማነጋገር ተጨማሪ (supplement) ቫይታሚን ዲ እንዲሰጠዉ ይጠይቁ:: ለልጆች ሌላ የቫይታሚን ዲ ማግኛ አማራጭ የቫይታሚን ዲ ምንጭ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የሆነዉ የፀሃይ ብርሃን ነው:: እርስዎም ልጅዎን ቫይታሚን ዲ ለልጅዎ መስጠት ካልቻሉ እንደ አማራጭ ሁልጊዜ ቢያንስ በሳምንት ሶስት ጊዜ የጠዋት የፀሀይ ብርሃን ማሞቅ ያስፈልጋል:: ስለሆነም በየቀኑ የጠዋት የፀሃይ ብርሃን ሙሉ ሰዉነቱን ከሆነ ከ10-15 ደቂቃዎች ማሞቅ የሚያስፈልግ ሲሆን ጭንቅላቱን፣ እጅና እግሮቹን ብቻ የሚያሞቁት ከሆነ ደግሞ ለ30 ደቂቃዎች ያህል ማሞቅ ያስፈልጋል:: ፀሃይ ሲያሞቁ ምንም አይነት የፀሃይ መከላከያ ልጅዎን መቀባት አያስፈልግም:: በተጨማሪም ልጅዎን ማሞቅ ያለብዎ ቀጥታ በፀሃይ ብርሃን ዉስጥ ነዉ፤ በመስታወት ዉስጥ የሚገባ የፀሃይ ብርሃንን ፈፅሞ አይጠቀሙ::

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# መፈንቅለ ስም (ወግ)

በደስታ ተከስተ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

ስምን መላዕክ ያወጣዋል ሲል አጐቴ ታዬር… መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ ትላለች እህት ኤሊፍ የሁለቱን አባባል በጥሞና የተከታተሉት ኢትዮጵያዊው… አለቃ አድባሩ «ለመላዕክት ያለ ግብሩ ግብር መስጠት አግባብነት የለውም ታላቁ የክርስቲያኖች መፅሐፍ እንደሚያስረዳን ከሆነ የመላዕክት ሥራ በፈጣሪ ታዘው የሰው ልጆችን መጠበቅና ማገዝ መሆኑን ነው።

ደግሞስ መልከ ጥፉን በቆንጆ ስም ቢጠሩት… ሽንገላ ካልሆነ በቀር ምን ፋይዳ አለው። በማለት አለቃ አድባሩ ያስረዳሉ። አለቃ ነገራቸውን ሲቀጥሉ… በሀበሻ ምድር ስም አወጣጥ ማን እንደ ጐጃሜዎች ትክክለኛ የስም አስያየምን ተክነውበታል። ለእነርሱ ያለኝ አድናቆትና ከበሬታ የላቀ ነው። ምነው እኔም ከጐጃም ተወልጄ ቢሆን ኖሮ… በማለት የግል አመለካከታቸውንና ስሜታቸውን… ያንፀባርቃሉ። አለቃ እንደሚናገሩት እኔም ለጐጃሜዎች ስም አወጣጥ አድናቆቴ የላቀ ነው… የስሜን መጠሪያ ትርጓሜው ግራ ቢያጋባኝና ውስጤን እየከነከነ ጠዋት ማታ ሀሳብ እየሆነብኝ ስለሆነ አብዮታዊና ስር ነቀል የሆነ የስም ለውጥ ለማድረግ ተነሳሁ።

መጠሪያ ስሜን ማን እንዳወጣልኝ አይታወቅም በመላዕክትም ሆነ በጐጃሜዎች የስም አወጣጥ ቀመር ውስጥ ፈልጌና አፈላልጌ አላገኘሁትም:: የስም ለውጥ የማደርገው በመርህ ላይ ተመስርቼ መሆኑን ይታወቅልኝ ዘንድ ለውድ አንባቢዎች እንደሚከተለው ለማብራራት እሞክራለሁ። ምን አልባት ከእኔ መጠሪያ ስም ጋር ተመሳሳይ ስም ያለው አንባቢ ቢገኝ የግሉን አመለካከት የማንፀባረቅ ህገ-አንባቢያን መብቱ የተጠበቀ መሆኑን መረዳት ይገባዋል። እኔም የፃፍኩት ህጉ-የመፃፍ መብቴን ተጠቅሜ ነውና!…

የዓለም ሀያል ሀገር የሆነችው አሜሪካ ከአውሎ ነፋስ የፈጠኑት በራሪ ጀቶቿ በኢራቅና በሶሪያ ሰማይ ላይ ያለ ከልካይ እየፈነጩ ISIS የተባለውን አሸባሪ ቡድን ላይ ቦንብ ሲያዘንቡ በእየለተ ዜና እየሰማሁ… የናይጀሪያ ኮማንዶ ጦር ሰራዊት ስናይፈር የተባለውን ጠመንጃ ታጥቆ ቦከሀራም የተባለውን አሸባሪ ሀይል ለመደምሰስ ዱር ቤቴ ማለቱን እየሰማሁ… የኢትዮጵያ መድፎች የአልሸባብ ታጣቂ ቡድን ለመደምሰስ… በሶማሊያ በረሃዎች አረር ሲተፉ እየተመለከትኩ… የዓለም መንግስታት እየተሰበሰቡ ጡንቻቸውን ለማፈርጠም በሚመክሩበትና ህግ እያወጡ በሚፈርጁበት ወቅት ላይ በፍፁም እኔ አሸብር ተብዬ መጠራት አልፈልግምና ስሜን ለውጫለሁ።

አጐቴ በኖረበት ዘመን በባህሪው ከሰዎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ ነዋሪ አልነበረም። የዛሬን አያድርገውና እርሻ ሲያርስ ድንበር (ወሰን) ገፊ… ሲመሽ የሰው በረት ከፋች… ሰርቆ አዳሪ… የሰው ሚስት አጫዋች ነበር ይባላል። በዚህ ዘሟች አመሉ ከዕለታት በአንዱ ቀን የገዛ ባልጀራውን ሚስት ሲያማግጥ ተገኝቶ በገዛ ጓደኛው መገደሉን የህይወት ታሪኩ ያስታውሳል። በወቅቱ እንደ ማህበረሰቡ አመለካከት ከቤተሰባችን የአጐቴን ደም… የሚበቀል ሰው ባለመኖሩ እናቴ ገዳይ የተባለውን ሰው ባየች ቁጥር ትበሳጭ ነበር። ይህ ከሆነ ከጥቂት አመታት በኋላ እኔ ተወለድኩ። እናቴ በሆዷ ፅንስ ብቻ አልተሸከመችም ለአመታት በልቧ ቂም ቋጥራ ስትኖር ነበርና ቁጭቷን ለመገላገል… ስትሻ መጠሪያዬን ደመላሽ ስትል ሰየመችው:: አስቡት እስቲ እናንተዬ… አጐቴ በገዛ ምግባሩ የዘራውን ባጨደ እኔ ምን ተበድዬ ደም አፍሳሽ ልሁን… ደግሞስ በጋርዮሽ በሚኖር ማህበረሰብ መካከል እንዲህ ያለ ችግር መከሰቱ መቼም የሚያጋጥም ነውና ደምን በደም ከማለት ደምን በእርቅና በይቅርታ መመለስ ይቻል ይመስለኛል እናም እባካችሁ ከእንግዲህ ደመላሽ… ደምሳሽ… በሚል ስሜ እንዳትጠሩኝ አሳስባለሁ። በእርግጥ አንዳንድ የሥራ ባልደረቦቼ እንደሚሉኝ ከሆነ «ስምህን ስንጠራው አፋችን ላይ ደም ደም… ይለናል… ምን አለበት ደመላሽ በሚለው ከምትጠራ… ለደም ባንክ ደም በመለገስ የክብር አባል ብትሆን…» ማለታቸውን አስታውሳለሁ።

ከእለታት በአንድ ቀን የአካባቢያችን ካድሬ መንደርተኛውን ሰብስቦ ስለ ሰላም አስፈላጊነት… ይናገራል «ሰላም ለአንዲት ሀገር ወሳኝ ነው ሰላም ከሌለ ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም አይታሰብም የአካባቢያችን ሰላም እንዳይደፈርስ ነቅተን መጠበቅ አለብን:: /ሰላማችን ከደፈረሰ ልማታችን ይስተጓጐላል ልማት ከሌለ ደግሞ እያንዳንዳችን በድህነት ማጥ ተዘፍቀን መቅረታችን… ነው። ይህን አወቀን የአካባቢያችን ሰላም እንዳይደፈርስ… / ለሰላማችን ነቅተው የሚሰሩ ኮሚቴዎች ከመካከላችን መምረጥ አለብን»… ብሎ ከጨረሰ በኋላ ከተሰብሳቢው አንዱ እጁን አወጣ እድሉ እንደተሰጠው… «መልካም ነው ሰላማችን እንዳይደፈርስ በንቃት ይሰራሉ ብዬ ከማምንባቸው አንዱ… አቶ አደፍርስ… ነውና እርሱ ቢመረጥ ጥሩ ነው» ሲል… በዚህ ጊዜና ካድሪው ተሳስቶም ይሁን አውቆ ባይገባኝም ስሙ በራሱ አደፍርስ የሆነ ሰው ለሰላም ኮሚቴ እጩነት ማቅረብ ምን ማለት ነው። ሲል አንዳንዱ ሲስቅ አንዳንዱ የእኔን ሁኔታ ለመመልከት ፊቱን አዞረብኝ። ከዛን ቀን ጀምሬ የስሜ ትርጓሜ ስላበሳጨኝ አደፍርስ የሚለውን ስሜን አስቀይሬያለሁ።

የሰዎች ሰባአዊ መብት እየተከበረባት ያለች ሀገር ነው ያለነው እየተባለ ጠዋት ማታ ሲነገር እየሰማሁ!… የአለም ሰባአዊ መብት ተሟጋቾች ስሜን እንዲያብጠለጥሉት ስለማልፈልግ ሰው ክቡር ፍጥረት መሆኑን ተገዝቢያለሁና… ከፈጣሪስ ጋር ተጣልቼ ነፍሴ በሲኦል ስለምን ትሰቃይ… ስለሆነም የስም ለውጥ አድርጌአለሁና በላቸው በሚለው ስሜ አልጠራም።

የኑሮ ውጣ ውረድ በየጊዜው ያስጨንቀኛል ስለ ነገ አትጨነቁ ቢልም መፅሀፉ… እኔ ግን ነገን በመፍራት አስባለሁ። እጨነቃለሁ… ብዙ ነገሮች ያስጨንቁኛል። የመኖሪያ ቤት እጦት… የሥራ ማጣት… የልጆች ቀለብና አልባሳት… ከጐረቤቶቼ ጋር ያለኝ ማህበራዊ ኑሮ… ከፍ ሲል ስለ ሀገርና ወገን ጭንቀት አለብኝ። በእንደዚህ አይነት እኔ እራሴ ጭንቀታም ሰው ሆኘ ስላለሁ እንዴት አስጨናቂ በሚለው ስሜ ትጠሩኛላችሁ?

ፍፁም ፈጣሪ ብቻ ነው። ሁሉን አዋቂና የሚሳነው ነገር የሌለ… እኔ ግን የቤታችን መብራት ገመዱ ተቆርጦ መቀጠል አቅቶኝ በጨለማ ብዙ ቀናት ቤተሰቤ ማደሩን ሳስብ ምንተስኖት የሚለው መጠሪያዬ… ይገርመኛል። ይህንም አስቀይሬያለሁ።

የእኔን አገልግሎት የሚፈልጉ በዙሪያዬ ብዙ ሰዎች አሉ እነርሱን ባገለገልኩ ቁጥር የኔም ተጠቃሚነት የዚያን ያህል ሰፊ ነው። ለሁሉም ዝቅና ትሁት ሆኘ ማገልገል ስለምፈልግ። ስሜ ተፅኖ እንዳይፈጥርብኝ ኩራባቸው… ናቃቸው… ተዋቸው… በሚለው ስሜ እንዳትጠሩኝ አደራዬ የጠበቀ ነው።

በሰፈራችን የጐረምሶች ጠብ ሲነሳ የመጀመሪያው ተደብዳቢ እኔ ነኝ ጓደኞቼ ከባላንጣዎቻችን ጋር ሲፋለሙ እኔ ግን እግር አውጭኝ ይቀናኛል ታናናሽ ወንድሞቼ ተደብድበው ሲመጡ እንደ ታላቅነቴ አለኋችሁ ማለት ያልቻልኩ ሰው በየትኛው ሞራሌ ደፋሩ… ሽመክት… ሽመልስ ጋሻዬ ወንድይራድ በሚለው ስያሜ ልጠራ? ስለዚህ የስም ለውጥ አድርጌያለሁ።

ችግርና ችጋር አድቅቆኝ አማራጭ በማጣት ለልመና ጐዳና በመውጣት ህይወቴን እገፋለሁ። አንዳንድ ነገሮች መለኪያ እንዳላቸው አውቃለሁ ለአብነትም የክብደት መለኪያ ሚዛን የርዝመት መለኪያ ሜትር… ሲጠቀሱ… የድህነት ዋነኛ መለኪያው አለም ባይስማማበትም እኔ መሆኔን አልጠራጠርም። በልመና ኑሮዬ ብዙ ገጠመኞች ቢኖሩኝም ዘወትር እኔን የሚያሸማቅቀኝ አንድ ነገር ነው:: አንዳንድ መፅዋች ተብዬ ሰው ቢራውን እየተጐነጨ… ስጋ የበላበትን ጥርሱን በእስትኪኒ እየጐረጐረ… ስለመድሐኒአለም ብዬ እጄን ስዘረጋለት አስር ሳንቲም ለመወርወር ደርሶ ስምህ ማን ይባላል? ብሎ ሲጠይቀኝ መቼስ የተጠየቁትን በአግባቡ መመለስ ምንም ለማኝ ብሆን የጨዋ ደንብ መሆኑን አውቃለሁና ሀብታሙ እባላለሁ ብዬ ስናገር ከጣሪያ በላይ እየሳቀ ሀብታም ታድያ ይለምናል እንዴ እያለ ይሳለቅብኛል ከዚህ የተነሳ ያለፍርድቤት ፈቃድ ቢሆንም ስሜን አስለውጫለሁ።

> የቤታችን መብራት ገመዱ ተቆርጦ መቀጠል አቅቶኝ በጨለማ ብዙ ቀናት ቤተሰቤ ማደሩን ሳስብ ምንተስኖት የሚለው መጠሪያዬ… ይገርመኛል።

በስሜ የተነሳ ከምወዳትና እንደራሴ አድርጌ ከምሳሳላት ፍቅረኛዬ ጋር ሰሞኑን ቅራኔ ውስጥ ገብተናል:: እርሷ እንደምትለው ከሆነ «እኔ ያፈቀርኩትን ሰው አቆላምጦ ለመጥራት የታደልኩት አልጋ ላይ ብቻ ነው። በሰው መሀል ላቆላምጥህ አልቻልኩም ያፈቀሩትን ሰው ስም በሰው ፊት አቆላምጦ በመጥራት የሚገኘውን ደስታ ለማጣጣም ስለምፈልግ ስምህን ካላስቀየርክ እየወደድኩህም ቢሆን ልለይህ እገደዳለሁ። ስላለችኝ የፍቅረኛዋ ስም ለማቆላመጥ ስላለተመቻት ተለያዩ የሚለውን ሀሜትና አሉባልታ ከመፍራትና በይበልጥም እርሷን ማጣት ስለማልፈልግ በድሉ በሚለው ስሜ ላይ መፈንቅለ ስም ማድረጌን አረጋግጣለሁ።

ውድ አንባቢዎቼ መቼም ፅሁፍ ያለ ርዕስ ሰውም ያለ መጠሪያ ስም አይሆንምና… በተቀየረው ስምህ ምትክ አዲሱ መጠሪያ ስምህን አስተዋውቀን ማለታችሁ ታውቆኛልና… እንደ ተገነዘባችሁት ጥልቅ የሆነ አብዮታዊ የስም መታደስ… አድርጌያለሁና እንግዲህ ዘመኑ በጥልቀት የመታደስ… እድል ፈጥሮልኛልና ህዳሴና ታደሰ በሚሉት ስሞች ብጠራ ፈቃደኛ መሆኔን በመግለጥ እሰናበታለሁ። ሰላም።

# Expediting the completion of research projects and raising their quality

By Yinager Teklesellassie (PhD), Faculty of Humanities

Guided by its vision to be one of the top research universities in Africa in a decade or so, the administration of BDU has been encouraging professors to do research which can solve local or national problems. As a result, the number of projects that have been funded by faculties or research institutes of the university has been increasing annually. Obviously, providing funding for research projects is the easiest part of the whole process of doing research. The most important thing is to monitor the execution of research projects so that they are completed in time and with high quality. As we know, most research projects funded by faculties or research institutes at BDU drag on for years and their quality may be questionable. For example, in the faculty, which the writer knows well, only a couple of completed research projects were presented at Friday seminars over the last two years. Similarly, there were only few papers presented at the annual research conference by professors in my faculty in the same period. This clearly shows that the gap between research projects funded and those completed in time has been huge. Definitely, we need to narrow the huge gap between the number of research projects that are funded and the ones that are completed in time. We also need to find ways which can improve the quality of most of the research projects that are conducted by our professors.

... some of us may not have the kind of skill needed to finish research projects in time and with the kind of quality required.

One may cite a number of reasons for the sluggish completion of research projects at BDU. The major reason is that all professors of the university are engaged in teaching, which leaves them very little time for other engagements like doing research. The other reason is that some of us may not have the kind of skill needed to finish research projects in time and with the kind of quality required. Still, some of us may decide to do research not because we truly want to solve a problem or to add knowledge to the existing body of knowledge in our discipline, but it is because we can't resist the lure of getting a large research funding which we can use for our personal needs.

Some simple steps can be taken to reverse this bad trend. The first step could be to notify every 'researcher' of the time when they are expected to submit progress reports and final reports. If any researcher does not comply with the notification, then any funding faculty or research institute can take very strict measures like withholding research funding for a new research project until the project work is completed. I believe that such measures may make researchers be more committed and complete their projects in time.

Equally important in raising the quality of the research projects completed, faculties or research institutes can also take some practical measures. For example, researchers need to be notified in advance that unless they publish their research articles in a reputable journal, they will not be allowed to get another research funding. If publishing is found to be difficult, however, presenting a paper at a national or international conference can be taken as mandatory to increase the quality of the funded research projects. In my opinion, these measures will help reward hardworking professors who are more interested in the creation of knowledge and solving practical problems.

In addition to encouraging the professors of the university to do research by providing funding, the university administration should take very concrete measures to speed up the completion of research projects in time and with the highest quality possible. Funding research projects alone will not get us where we want to be in under ten years' time.

# The Untold Stories of College of Health Sciences

**By Wendemagegn Enbiale (MD, MPH)**
**Dermatovenerologist,**
**College of Medical and Health Science**

Working in universities as a teacher and as a health professional has many things in common. Both jobs require humble, confidential and ethical professionals. In these two professions, the lives of people are emphasized over private issues. If you are working for a university as a teacher, your workload might include 2.4 hours of teaching, 4.8 hours of preparation/reading and 36 minutes of community service and research. Although both share some similarities, these working areas are also diverse worlds in many ways. Therefore, in my reflection today, I will emphasize the uniqueness of medical sciences by pointing out the untold stories of health sciences at BDU.

To begin with, the hospital is always busy with an average of 600 outpatient and 400 inpatient consultations, 20-25 major surgeries, 15 to 20 gynecologic and obstetric surgeries, more than hundred pediatric and neonatology consultations. All cases of medical treatments from the specialty clinics and procedures and the emergency health services are also provided by the physicians of the health science college. Further, the typical day of the college physician life can go from 8 hours to 36 hours working back-to-back rapid-fire meetings. They begin the day by a morning meeting( those who do not have class to teach ) to discuss on the overnight cases , then doctors start seeing patients for consultations need a special care. In the consultation clinic, they freshen up on the details of the case, try and get a sense of what's going on for the students and nurses, and then work on with a plan to investigate the management for 20 minutes. The hospital expects every physician to see 30 to 35 patients per day. If they are scheduled to do surgery, they are expected to start their day as early as 7a.m, wearing all the gadget of infection prevention. Suffocated with the warm Operation Room temperature and back to back 5 to 7 major operations, some of them may continue for hours and in most days without lunch.

Last year, when public health emergencies were prevalent in the country due to the El Nino effect, it was our physicians who voiced the alarm and secured 150,000,000 birr worth of medicine by managing more than 852,000 scabies cases. Moreover, in August, following the report of acute watery diarrhea in Bahir Dar, 13 dedicated university physicians have worked day and night in Addis Alem Hospital. Accordingly, they helped the hospital in reducing the patient number from 450 to 15 in less than 10 days.

continued on page 15

# እንግዳችን

## “ለነገ ሃገር ተረካቢ ለሆኑ ህጻናት ምቹ፣ ለአካልና ለአእምሮ እድገታቸዉ ተስማሚ የሆነ ከአደጋ የጸዳ የመዋያ አካባቢን ለመፍጠር ነዉ፡፡”

ሲስተር ኤደን አምሣሉ

**የዚህ ወር እንግዳችን በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርት እና አዲስ የተከፈተው የሕፃናት ማቆያ ኃላፊ የሆነችው ሲስተር ኤደን አምሣሉ ናት፡፡ ሲስተር ኤደን የህይወት ተሞክሯዋን ልታጋራን ከናይል ጋዜጣ ዘጋቢ ሙሉጐጃም አንዱአለም ጋር ቆይታ አድርጋለች፤ ቃለ መጠይቁን እነሆ፤ መልካም ንባብ!**



ናይል፡- በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንሽ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰገን ሙሉ ስምሽን፣ የትውልድ ቦታና የአስተዳደግ ሁኔታሽን ብትገልጭልን?

ሲ/ር ኤደን፡- ስሜ ኤደን አምሳሉ ይመር ይባላል፡፡ የተወለድኩት ጎንደር ከተማ ቀበሌ 03 ሲሆን እስከ 9 አመቴ ድረስ እዛዉ ነዉ ያደግሁት፡፡ ከዛ በሁአላ ግን እናቴ ለስራ ባህርዳር ከተማ በመመደቧ ምክንያት ቀሪዉን የልጅነት ጊዜየን ያሳለፍኩት እዚሁ ባህርዳር ከተማ ነዉ፡፡

አባቴ በልጅነቴ ነዉ ከእኛ የተለየዉ እና ለእናቴ ብቸኛ ልጅ ነኝ ስለዚህ ከእናቴ ጋር ብቻ ነዉ ያደግሁት፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን የተማርኩት “ባህርዳር ካቶሊክ ትምህርት ቤት” ሲሆን የመሰናዶ ትምህርቴን ደግሞ ያጠናቀቅሁት “ ባህርዳር የመሰናዶ ትምህርት ቤት” ነዉ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በ2001 ዓ.ም በመደወላቡ ዩኒቭርሲቲ እንዲሁም የሁለተኛ ዲግሪዬን በ2005 ዓ.ም ጎንደር ዩኒቨርሲቲ አጠናቅቄያለሁ፡፡

አስተዳደጌ ምንም የተለየ ነገር የለዉም፡፡ ብቻ እናቴ በራስ መተማመን እንዲኖረኝ ከልጅነቴ ጀምሮ እንደትልቅ ሰዉ እያየችኝ ፤ በራሴ እንድወስን እያደረገችኝ፤ ሃላፊነቶች እየሰጠችኝና እምነት እየጣለችብኝ ነዉ ያሳደገችኝ፡፡ ይህ ደግሞ ለዛሬዉ ማንነቴ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጎአል፤ ስለዚህ እናቴን ለዚህ አስተዋይነቷ ሳላመሰግናትና ሳላደንቃት አላልፍም፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን መቼ ተቀላቀልሽ? ከዩኒቨርሲቲው ውጭ የሰራሻቸው ስራዎች ካሉ ብትገልጭልን?

ሲ/ር ኤደን፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን የተቀላቀልኩት በ2003 ዓ.ም የካቲት ወር ነዉ፡፡ ከዚያ በፊት የመጀመሪያ ዲግሪዬን እንደተመረቅሁ የተመደብኩት ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ነበር፤ አንድ አመት ከ6 ወር አስተምሬ ነዉ ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተዛወርኩት፡፡

ናይል፡-በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከማስተማር በተጨማሪ ያለሽ ኃላፊነት ምንድን ነው?

ሲ/ር ኤደን፡- በአሁኑ ጊዜ ከመማር ማስተማሩ ዉጪ አዲስ በተከፈተዉ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህጻናት ማቆያ ሃላፊ ሆኜ አገለግላለሁ፡፡

ናይል፡- የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለረጅም ጊዜያት በጉጉት ይጠብቀው የነበረው የህፃናት ማቆያ ማዕከሉን እውን በማድረግሽ በቅድሚያ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንኳን ደስ አለሽ እያልን ማዕከሉን ለማቋቋም የቤተሰብሽ ሁኔታ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ እስቲ ስለ ቤተሰብሽ አጫውችን?

ሲ/ር ኤደን፡- ባለትዳርና የሁለት ልጆች ማለትም የአንድ ወንድ እና የአንድ ሴት ልጅ  እናት ነኝ፡፡ ባለቤቴ እዚሁ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር ነዉ፡፡ ቤኛ ቱሉ ይባላል፡፡ የቤተሰብሽ ሁኔታ አስተዋጽኦ አለ ወይ? ላልሽዉ አዎ፤ በአለማችን ያሉ አብዛኞቹ መፍትሄዎች የመነጩት ከችግር እንደመሆኑ መጠን እኔም የመጀመሪያ ልጄን ሳሳድግ ሰራተኛ በማጣት ተቸግሬአለሁ፡፡ ሁለተኛዋን ስወልድ ደግሞ ባለቤቴ ለሶስተኛ ዲግሪ አዲስ አበባ ሄደ፤ በዛ ላይ የትምህርት ክፍላችን የሰዉ ሃይል እጥረት ነበረበት፡፡ ስለዚህ ሥራዉና ባብዛኛዉ ልጅ የማሳደጉ ሃላፊነት የኔ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት እስከመቼ በሰራተኛ ተማምነን እንኖራለን ብየ አስብ ነበር፡፡ ሰራተኛ ባለኝም ጊዜ ቢሆን ለአንዲት ያልተማረችና፤ የእናትነት ልምድ ለሌላት ብሎም ምንም ተጠያቂነት ለማይኖራት ምናልባትም ከ18 አመት በታች ለሆነች ልጅ ምቹ ባልሆነና ለአደጋ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች በሞሉበት የመኖሪያ አካባቢ ልጄን ጥዬ መዋል ለኔ ትልቅ ፈተና ነበር፡፡ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማኝ ነበር ሁልጊዜ በስራና ከልጄ ጋር በመሆን መካከል እንደተወጠርሁ ነበር፡፡ ስለዚህ በስራ ሰአት ግዴታ የሆኑብኝን የስራ ሀላፊነቶች ብቻ ከዉኜ ነበር በቶሎ ወደ ቤት የምሮጠዉ ካልሆነም በሀሳቤ ቤት ነኝ፡፡ ይህን ከስራም ከቤትም ያለመሆንን ስሜት አልወደዉም፡፡ ደግሞም አብዛኞቹ በስራ ላይ ያሉ እናቶች የሚጋሩኝ ስሜት ነዉ፡፡ ይህ ሁኔታ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህጻናት ማቆያ ቢኖር የሚለዉን ጽንሰ ሀሳብ እንዳመነጭ አድርጎኛል፡፡

በሃሳቤ እንድገፋበት ያደረገኝና ለስኬት ያበቃኝ የቤተሰብ ሁኔታ ደግሞ የባለቤቴ ድጋፍ ነው፡፡ ገና ሳስበዉ ጀምሮ ነው ያማከርኩትና ያበረታታኝ የነበረዉ ከዛም እስከ መጨረሻዉ ድረስ እዚህ ባህር ዳር በተገኘበት ጊዜ ሁሉ አግዞኛል፡፡ እንደዉም አንድ ገጠመኝ ልንገርሽ የማቆያዉን ምንጣፍ በምናስነጥፍበት ጊዜ የሚያነጥፉትን ሰዎች ቀጠሬ እኔ ሌላ ሃላፊነት ስለነበረብኝ ባለቤቴን ነበር እንዲያስተናግድልኝ የጠየቅሁት፡፡ ሲያነጥፉ ሲሉ ግን ወለሉ እንደ አዲስ መጸዳት ነበረበት እናም የጽዳት ሰራተኛ ወዲያዉ ማግኘት የማይቻል ሲሆን መጥረጊያ ከጎረቤት ካለ ካፌ ተዉሶ ቤቱን በሙሉ ራሱ ጠርጎ አስነጥፎ ጠበቀኝ፡፡ ይህ ማለት ለኔ ትልቅ ነገር ነዉ፡፡ ለኔ ብቻም አይደለም ለማንኛዋም ሴት የባለቤቱዋ ድጋፍ ከሁሉ ነገር በላይ ነዉ፡፡



ናይል፡- በዩኒቨርሲቲው ማዕከሉን ማቋቋም ለምን አስፈለገ?

ሲ/ር ኤደን፡- ማእከሉ የተቋቋመበት ዋነኛ አላማ የዩኒቨርሲቲዉ ሴት መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ሙሉ አትኩሮታቸዉን ስራቸዉ ላይ ማድረግ እንዲችሉና ዉጤታማ እንዲሆኑ  ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ የሴቶች ተሳተፎ አነስተኛ በሆነበት የአመራር ቦታ፣ ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት የተሻለ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ነዉ፡፡ ሌላዉ ደግሞ ለነገ ሃገር ተረካቢ ለሆኑ ህጻናት ምቹ፣ ለአካልና ለአእምሮ እድገታቸዉ ተስማሚ የሆነ ከአደጋ የጸዳ የመዋያ አካባቢን ለመፍጠር ነዉ፡፡

ናይል፡-የማዕከሉ መቋቋም በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ላይ የፈጠረው ስሜት እና አቀባበል ምን ይመስላል?

ሲ/ር ኤደን፡- በጣም ደስ የሚል ነበር፡፡ አይደለም የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ በተለያየ አጋጣሚ የሰሙ ከዩኒቨርሲቲዉ ዉጭ ያሉ ሰዎች እንኳን በጣም ነዉ የተደሰቱት፡፡ በቂ ጥናት አድርጌአለሁ ብየ ባላስብም፡፡ በተለያየ አጋጣሚ ካገኘሁአቸዉ የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብና ከህጻናቱ ወላጆች ያገኘሁት ምላሽ ከጠበቅሁት በላይ ነዉ፡፡ ብዙዎቹ እዉን የሚሆን እንዳልመሰላቸዉ፣ በጣም አስፈላጊ እና ብዙ እናቶችን ከጭንቀት የሚገላግል እንደሆነ ገልጸዉልኛል፤ እንደ ጀማሪነቱ ደግሞ የተቋቋመበትን ፍጥነትና ጥራት ሁሉም ማለት ይቻላል በጣም ደስ የሚልና ከጠበቅነዉ በላይ ነዉ ብለዋል፡፡ እንደዉም ከደስታ ብዛት ያለቀሰች ባልደረባዬም ነበረች፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ወደ 90 እናቶች ማመልከታቸዉና በጊዜዉ ማስተናገድ የቻልነዉ 30ዎቹን ብቻ በመሆኑ ቀሪዎቹ እናቶች አዝነዋል፡፡ እንደዉም እድሉን የሰጠነዉ በእጣ እንደመሆኑ መጠን እጣዉን አንስተዉ ዜሮ ሲወጣላቸዉ ፊታችን ላይ እየወረወሩ የሄዱ እናቶች ነበሩ፡፡ ይህ ሁኔታ እኔንም አሳዝኖኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እስከ አሁን ድረስ ማቆያዉ ለመምህራን ብቻ የሚመስላቸዉ ሰዎች አሉ፡፡ ነገር ግን ማቆያዉ ለማንኛውም ሴት የዩኒቨርሲቲዉ ሰራተኛ መሆኑን አሁንም በድጋሚ ማሳወቅ እፈልጋለሁ፡፡ ሌላዉ ደግሞ የወንድ የዩኒቨርሲቲዉ ሰራተኞች ለምን ለሴት ብቻ የሚል ጥያቄ ነዉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ በአመራር ቦታ ላይ የተቀመጠ የዩኒቨርሲቲዉ ሰራተኛ የሰጠኝን አስተያየት አስገርሞኛል አሳዝኖኛልም፡፡ እንዲህ ነበር ያለዉ “ለዚህ እኮ ነዉ ሴቶችን የምንጨቁናችሁ፤ ትንሽ ለቀቅ ስትደረጉማ አትቻሉም፡፡”

ይህ ዉሳኔ ወንዶችን ለማግለል ሳይሆን ካለብን የቦታ ዉስንነት እና ከተቋቋመበት አላማ አንጻር ቅድሚያ መስጠት ሰላለብን ነዉ፡፡ ይህ የኔ (የሴት) ዉሳኔ ሳይሆን የማኔጅመንት ዉሳኔ ነዉ፡፡ ዉሳኔዉ ደግሞ ማስፋፋቱንም ስለሚጨምር በቅርቡ

# እንግዳችን ...

መፍትሄ ይገኝለታል ብዬ አስባለሁ እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ፡፡

ናይል፡- ማዕከሉን ለማቋቋም ብዙ ውጣ ውረዶች እንደነበሩ እኤም አስታውሳለሁ፡፡ እስቲ እነዚህ ውጣ ውረዶችን እናንሳቸው?

ሲ/ር ኤደን፡- ስለ ዉጣ ዉረዶቹ ከማንሳቴ በፊት ስለነበሩት መልካም ነገሮች ባነሳ ደስ ይለኛል፡፡ በቅድሚያ የዩኒቨርሲቲዉን ማኔጅመንት ቀናነት ማንሳት ይኖርብኛል፡፡ በርግጥ የፕሮጀክቱን ተግባራዊነት እስኪያምኑበት ድረስ ትንሽ አመላልሰዉኛል፡፡ ከተቀበሉት በኃላ ግን የከለከሉኝ አንዳች ነገር አልነበረም፡፡ በተለይ ፕሬዘዳንት ጽ/ቤቱን ከልብ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ለህጻናት ማቆያዉ ያስፈልጋል ያልሁትን ነገር በሙሉ ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡ በተለይ በእኔ ላይ የነበራቸዉ እምነትና ማበረታታት የትኛዉንም ዋጋ ከፍዬ እንዳላሳፍራቸዉ ያነሳሳኝ ነበር፡፡ ከዚያ በተረፈ የደረስኩባቸዉ የዩኒቨርሲቲዉ አመራሮች በሙሉ በታላቅ አክብሮትና ቅንነት ነበር ያስተናገዱኝ ስለዚህ እግዚአብሄር ያክብርልኝ እላለሁ፡፡ ሌላዉ ጥሩ ነገር ደግሞ ሥርአተ ጾታ ዳይሬክቶሬት በሁሉ ነገር ከጎኔ ሆነዉ የጠየኩአቸዉን ነገር ሁሉ ያደርጉልኝ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች በተለይ ደግሞ ሴቶቹ ሁልጊዜ ስለደረስኩበት ደረጃ ይጠይቁኝ ነበር፤ ምን እንርዳሽ ይሉኝ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ብቻዬን እንዳልሆንኩና እኔ ብተወዉ እንኳ የሚያስቀጥሉት ብዙ ሰዎች እንዳሉ አይቻለሁ፡፡

ስለ ዉጣ ዉረዶቹ እናንሳ ከተባለ ደግሞ ጥቂቶቹን ልናገር፡-

1ኛ፡- የመጀመሪያዉና ከባዱ ፈተና የሆነብኝ ያንን ቤት ማስለቅ ነበር፤ ምክንያቱም በአራት አካላት የተያዘ ነበር፡፡ ቦታዉ እንዲለቀቅና ለህጻናት ማቆያዉ እንዲሆን በደብዳቤ ከተላለፈና ዉስጡ ለነበሩት ተለዋጭ ቦታ ከተሰጠ በኃላ እንኳን በስተመጨረሻ ቦታዉን ለማስለቀቅ የበቃነዉ በግቢዉ ፖሊስ ጣልቃ ገብነት ነዉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ የዋናዉ ግቢ እቃ ግምጃ ቤት ባለሙያ አቶ ጥላሁንን ሳላመሰግን አላልፍም፡፡ የማይመለከተዉን እቃ ተረክቦ ነዉ ጉዳዩን እልባት የሰጠልኝ፡፡ አንዳንዴ ህግ ባያዝዘን የሚያስገድደን አካል ባይኖር እንኳ እንደዚህ ከመልካም ነገር ሁሉ ጎን የመቆም ልምድ ቢኖረን ጥሩ ነዉ፡፡

2/ ሌላዉ ከባዱና እልህ አስጨራሽ የነበረዉ ግዥዉ ነበር፡፡ የእኛ ሀገር የግዥ ሂደት የምታዉቁት ነዉ፡፡ ይህንን ሂደት ለማቅለል ግን ቀናነት የግድ አስፈላጊ ነገር ነዉ፡፡ ከሂደቱ መወሳሰብ በላይ ተደርበን እኛዉ የምናከብደዉ ከሆነ ግን የማይቻል ነዉ የሚሆነዉ፡፡ እኔን ያጋጠመኝ ይሄዉ ነበር፡፡ ከግዥ ባለሙያዎቹ አንድዋ እጣው በሚወጣበት ስብሰባ ላይ በአደባባይ “ማቆያዉ የመምህራን ብቻ ስለመሰለን ግዥዉን ሆን ብለን ይዘነዉ ነበር” ብላ ስትናገር ሰማሁ፤ ይህ ልብ የሚሰብር ነበር፤ ምክንያቱም በዚያ ጊዜ ሁሌም ቢሮአቸዉ ያለአንዳች እርባና እየተመላለስኩ ነበር ማለት ነዉ፡፡ ግዥዉን ማስቆም ካለባቸዉ እንኳ በግልጽ መሆን ነበረበት እንጂ ሰባሰበብ በመፍጠር አልነበረም፡፡ ይሄ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል አስተሳሰብ እስከዛሬም አልጠቀመንም ወደፊትም የትም አያደርሰንም፡፡ ይህን ስል ግን አብራን የደከመችዉን ወይዘሮ አዲስን ሳላመሰግን አላልፍም ምክንያቱም በእሷ መኖር ምክንያት ነዉ በመጨረሻም የተሳካዉ፡፡

3/. የጥገና ባለሙያ እጥረት ደግሞ ሌላዉ ችግር ነበር፡፡ ላሉት ዉስን ባለሙያዎች ደግሞ ይህ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ጉዳይ አልነበረም፡፡ ስለዚህ በመሃል በመሃል የሚገቡትን ስራዎች ሁሉ እስኪያልቁ መጠበቅ ግድ ነበር፡፡ ሲብስም በራሴ ወጪ ባለሙያ ቀጥሬ ያሰራሁበት ጊዜ ነበር፡፡

4. ሌላው እዚህ ግቢ ውስጥ በደብዳቤ የሚፈጸም ነገር የለም ማለት እችላለሁ፡፡ በእኔ ተሞክሮ እያንዳንዱን ጥቃቅን ነገር እያንዳንዱን ጉዳይ እኔ በአካል ተገኝቼ ካላስረዳሁና አንዳንዴም ካለመንኩ የሚሆን ነገር አልነበረም፡፡ ይህ ከማስተማር ጊዜዬ ውጭ ላለፉት ዘጠኝ ወራት በየቢሮው እየተንከራተትኩ እንዳሳልፍ አድርጎኛል፡፡ አሁን ጥበብ ሕንፃ ላይ የማያውቀኝ ሰው አለ ብዬ አላስብም፡፡ ለአንዳንድ የቢሮ ሰራተኞች ባለጉዳይን ከሰዓት ተመለስ ወይም ነገ ና ማለት በጣም ቀላል ነገር ነው፡፡

5. የመኪና ችግር ደግሞ በጣም ያለፋኝ ነገር ነው፡፡ ከእቃ ግምጃ ቤት፣ ከኢንተርፕራይዝ ፣ ከገበያ የተለያዩ እቃዎችን ወደ ማዕከሉ ለመውሰድና ግዥውን ለመፈጸም ብዙ ጊዜ መኪና ማስፈቀድ ነበረብን፡፡ ለዚህ ተብሎ የተመደበ መኪና ባለመኖሩ ስራ ላይ ያልሆነ መኪና መጠበቅ ነበረብን፡፡

6. እናም የአንዳንድ ሰራተኞች ቸልተኝነት እና ስራቸዉን በተገቢዉ ጊዜ አለመፈጸም፡፡ እነዚህ እንግዲህ ከብዙ ተግዳሮቶች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

ናይል፡- ማዕከሉን ለማቋቋም ባደረግሽው ጥረት ብዙ ጥሩም መጥፎም አጋጣሚዎች ነበሩሽ፡፡ ከእነዚህ አጋጣሚዎች ብዙ የተማርሽው ነገር በመኖሩ ለአንባብያን ብታካፍይ?

ሲ/ር ኤደን፡- የተማርኩትን ጠቅለል አድርጌ ስገልፀው ከምናስበው በላይ የሆነ አቅም እንዳለንና ሁልጊዜ ከአቅማችን በላይ ከፍ ብለን ማሰብና ማቀድ እንዳለብን ተምሬአለሁ፡፡ በዛ ላይ ቅንነት (being optimist) ምን ያህል ጉልበት እንዳለው ተምሬአለሁ፡፡ በግሌ ደግሞ ያሉኝን ጠንካራና ደካማ ጐኖች ተረድቼበታለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የትዕግስትን ፍሬአማነት አይቼበታለሁ፡፡

ናይል፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 በአፍሪካ ውስጥ ካሉ 10 ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ጐራ ለመሰለፍ የያዘውን ራዕይ ለማሳካት የሴት መምህራንና ሰራተኞችን ሚና ከፍተኛ ለማድረግ ማዕከሉ መቋቋሙ ሚናው ምንድን ነው?

ሲ/ር ኤደን፡- ሴት መምህራንና ሰራተኞች በሙሉ በስራ ሰዓት ስራቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ያደርጋል፤ በስራ ሰዓት ገብተው በስራ ሰዓት እንዲወጡ ያደርጋቸዋል፤ የልጆቻቸዉ ጤና እንዲጠበቅና ከስራ እንዳይቀሩ ያደርጋል ዩኒቨርሲቲው እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው” በሚል መንፈስ ሳይሆን ለሰራተኞች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚጥር ሲያዩ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው ያደርጋል፤ መምህራን ግዴታቸውን ከመወጣት ባሻገር በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት፤ በአመራር አገልግሎት እንዲሳተፉ ጊዜ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ የሴቶች ተሣትፎ ደግሞ ዩኒቨርሲቲው በ2017 በአፍሪካ ውስጥ ካሉ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ጐራ ለመሰለፍ የያዘውን ራዕይ ለማሳካትና የሴት መምህራንና ሰራተኞችን ሚና ከፍ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ሙሉ ያደርገዋል፡፡

ናይል፡- ይህ ማዕከል ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ገልፀሽልናል፡፡ የበለጠ ሁሉንም ለማርካት ምን መደረግ አለበት ትያለሽ?

ሲ/ር ኤደን፡- የሁሉንም ፍላጐት ለማርካት ብቸኛው አማራጭ ብዬ የማስበዉ በየ ካምፓሱ መክፈትና ይህንንም የተወሰነ ማስፋፋት ነዉ፡፡ ይህን ማድረግ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቀላል ወጪ ነው፡፡ ነገር ግን የብዙዎችን ጭንቀት የሚያቀልና ጥሩ ሀገር ተረካቢ ዜጐችን ለማፍራት የሚያስችል ነው፡፡

ናይል፡- በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊው መልዕክት ካለሽ እና ለማዕከሉ መቋቋም ጉልህ አስተዋፅኦ ያደረጉ አካላትን ማመስገን ትችያለሽ?

ሲ/ር ኤደን ፡- በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይፈቀድልኝ፡፡ በጎ ስጦታ ሁሉ ከላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ሳስብ በዋነኛነት አምኜ የተነሳሁት እግዚአብሔርን ነበር እርሱም አላሳፈረኝም፡፡ ከዚህ በመቀጠል የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት በተለይም ፕሬዘዳንት ጽ/ቤቱን፤ ከዛም ስርአተ - ጾታ ዳይሬክቶሬት፣ እያንዳንዱን የገባሁባቸውን ቢሮዎች በትህትና በትዕግስት ያስተናገዱኝን በሙሉ እንደ ምርምርና ማህበረሰብ ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት፤ ሰው ሀይል፣ ጥገና፣ ስምሪት፣ የእቃ ግምጃ ቤት፣ ቢዝነስና ልማት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት፤ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፤ ጠቅላላ አገልግሎት ሰራተኞችን በሙሉ ስራቸውን ባግባቡ ለመፈጸማቸው እና ከዛም አልፈው ለከፈሉት ዋጋ ሳላመሰግናቸው አላልፍም፡፡ ሰዓሊ እያዩ ገነት እና አሳዛር ማዕከሉን በስዕል በማስዋብ እና ለነበራቸው መልካምነት ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ አሁን አብረዉኝ እየሰሩ ያሉትን የህጻናት ማቆያ ሰራተኞች በሙሉ ከልቤ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ማቆያዉን እንደተቀጠሩበት ቤት ሳይሆን እንደቤታቸዉ አድርገዉ ነዉ የያዙት፡፡ ሁልጊዜም መሰረት መጣል አስቸጋሪ ነዉ፤ ሆኖም ከልባቸዉ ነዉ ማቆያዉን ስኬታማ ለማድረግ እየለፉ ያሉት፡፡ በስተመጨረሻ በሀሳብ ከፅንሰ ሀሣቡ ጀምሮ ጎበዝ በርች ብለው በእያንዳንዱ ደረጃ አይዞሽ እያሉኝ የነበሩትን ጓደኞቼና የሥራ ባልደረቦቼ በሙሉ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በተጨማሪ የማስተላልፈው መልእክት ይህንን እያነበቡ ላሉ ሰራተኞች በሙሉ በዚህ አጭር ጊዜ ዉስጥ አንዳንድ መስሪያ ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች እያደረጉት እንዳለዉ ተሞክሮዉን እንዲወስዱ እጋብዛለሁ፡፡

በቅርብ ቀን የተቋሙ የመክፈቻ ስነ ስርዓት ስለሚካሄድ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲታደም እጋብዛለሁ ፡፡

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍላችን ስም እናመሰግናለን፡፡

ሲ/ር ኤደን፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡





# The 70:30 Policy Dilemma: Resource Demands vis-à-vis the Policy

*Kibrom Mengistu (Department of Psychology, CEBS)*

As higher education is increasingly viewed as an instrument for economic development, there are pressures to create both more graduates and research opportunities in technological and scientific studies. Realizing the role of science and technology as a means to ensure fast and sustainable economic and technological development, the Ethiopian government adopted a new higher education policy in 2009 called the *70:30 program mix ratio*. To illustrate, 70% of the total undergraduate students enrolled in public universities go to natural science fields and the remaining 30% to the social science streams. 40% of students from the science stream have to go to engineering and 5% to medicine and health science.

For the past 6 years or so, therefore, the higher education system has witnessed a shift in focus from the lower cost studies in the humanities and social sciences to the higher cost studies in science and technology to produce more graduates in these costly fields. In fact, the dramatic shift of emphasis to science and technology fields is an expensive strategy that undoubtedly requires the construction and staffing of new higher education institutes as well as expansion of higher education opportunities, especially in those two fields that have been most restrictive and expensive studies traditionally: medicine and engineering.

Particularly, the 70:30 policy requires more resources to finance the construction of more classrooms, dormitories, laboratories, workshops and office for faculty; more resources for the recruitment and retention of competent and qualified academic staff in these fields of studies. It also requires far more resources to finance basic laboratory equipment, chemicals, computers, ICT infrastructure and practical training of students in these areas. Moreover, it requires the establishment of sufficient library resources and access to the vast reservoir of digitally stored documents and databases (e-books, e-journals, etc) available in electronic form. Needless to say, the consequences of such costly expansion have serious financial or cost implications.

### *How are we progressing?*

The 70:30 ratio target which was set to be achieved by the end of the first GTP period (2014/15) was reported as being successful. According to the Ministry of Education, the ratio has reached about 68:32 proportion in 2013/14. In a rush to materialize the 70:30 policies, however, we have begun to observe visible deficiencies. For instance, a number of the newly established universities that do not have adequate university facilities began to offer training in science and technology programs (such as medicine and engineering). Although training in these programs requires expensive lab equipment and sophisticated technology, many of these universities appear to be underequipped and not well-prepared to effectively run the training. What is worse, some of these universities are still struggling to fulfill the very basic physical resources (classrooms, offices, libraries, laboratories) required to provide optimum level of training.
As a result, students who study engineering, medicine, biology, chemistry, physics, etc from the underequipped universities have been urged to rely on other universities with better facilities in an effort to obtain facilities (laboratory, workshops, etc) and technical support. As an example, laboratories and workshops at Bahir Dar University have been used to serve students from Debre Tabor and Woldia universities. In addition, lab assistants and faculty from natural science departments often complain about the shortage of lab equipment, lack of laboratories and insufficient instruments. The large number of students that limited many students from conducting lab experiments simultaneously rather than sequentially doubles the problem. To the worst, ESDP V (Education sector development program V) also confirmed that the supply of teaching staff with postgraduate qualifications lacks pace with the increase in student enrolment. Consequently, large shares of undergraduate students have been taught by staff with a Bachelor degree.

The role of standardized laboratories, equipment, chemicals and computers for quality education is irrefutable. However, given that most new universities offer these courses below the minimum training standards of the programs, it is clear that it will have wider implications of dire consequences on the quality of education. In support of this, a study conducted by HERQA on employers' satisfaction revealed that engineering and medicine graduates were insufficiently qualified for the job. The survey found that there were visible deficiencies on graduates performance, especially in quality of work, specific job related knowledge and skill. The government priority areas of medicine and engineering have been the most dissatisfying to employers. This could make the government's plan of providing the economy with qualified manpower from the science and technology streams questionable.

According to ESDP V, the plan for the next 5 years was set to 'increasing *the number of institutes of technology and upgrading science and technology universities to international centre of excellence standards*'. Specifically, the government is committed to increase intake and enrolment capacity in public higher education institutions for undergraduate from the current 9.4% to 15%. This definitely necessitates strengthening the infrastructure and human resource capacity of the exiting universities for higher education enrolment. Hence, if university intake capacity continues to expand at the current rate, the government must ensure the availability of sufficient staff with appropriate skills to provide quality instruction, and hence attain the ultimate national goal.

### *Concluding remarks*

The higher education system in Ethiopia has generally been undergoing massive expansion that increases the number of universities and enrolments over the last two decades. This expansion will continue for the period of ESDP V. However, the current expansion has created serious financial pressures on institutions. The financial pressures become even more serious when we take the 70:30 policy shift into account as it demands costly resources in large quantity. Clearly, the 70:30 policy highly demands relatively costly scientific, laboratory and computing equipment and library materials as well as costly labor. Despite this financial context, the Ethiopian higher education system is still expanding, with 11 new universities set to be added soon. Such an expanded higher education system, however, needs the continuous and reliable support of the public revenue.

> In a nutshell, the pressures to raise the educational quality of universities for all students may require new ways of providing learning opportunities including the use of innovative instructional approaches, better use of technology, internships, access to ICT facilities, and so on.

While Ethiopian higher education system has been rapidly expanding especially in the fields of studies that demand costly resources, the prospects for the government to maintain vitality and reach competitive standard globally at present seem to be a bit far from achievable. This is mainly because the capacity of the nation to supply each institution with state-of-the-art educational, scientific and technological materials and equipment is somehow limited. Hence, institutions need to be

continued on page 14

# ፍናፍንት

## ምእራፍ ሶስት

በታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)
(www.facebook.com/ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ)
የ3ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ

አዲስ ሞዴል ሃይሉክስ መኪና ማሳውን ሁሉ እየጠረማመሰች አጤዳስ ስትደርስ የባለወልድ ንግስ እሚነግስበት ሜዳላይ ረግዶ ተይዟል። ራሄል ሹፌሯ ወርዶ በር እስኪከፍት ሳትጠብቅ ተስፈንጥራ ወርዳ እየተንሰቀሰቀች ወደ ለቀስተኞቹ ትሮጥ ጀመር። የቅርብ የቅርብ ዘመድ በደረሰበት ሃዘን መነፍረቁን ሳያቆም እያቀፈ ሰላም አላት። ከሁሉም ጋር እየተቃቀፈች እየየውን ታስነካው ጀመር። ለቅሶው ቤንዚህ እነደጨመሩበት እሳት ይብስ ተግለበለበ።

ራሄል የመጣችበትን መኪና ከቦሌ የረር በር ወደሚገኘው ቤቷ እየሽከረከረች ኢምፔርያል ሆቴል ጋር ስትደርስ የቦብ ማርሊ አደባባይን ወደቀኝ ዞራ ትንሽ እንደነዳች ስልኳ ጮኸ። እያሽከረከረች ስለነበር ለማንሳት ስላልተመቻት ጥግ ለመያዝ ስትነዳ ጥሪው አብቅቶ ተቋረጠ። አንድ ፊቱን ቤት ስገባ እደውልለሁ ብላ እየነዳች ማርያም ቤተክርስቲያን ጋር ስትደርስ በድጋሚ ስልኳ ድምፅ ስላሰማ ጥግ ይዛ ቆመችና አነሳችው።

"ሄሎው!"

"ሃሎ ምትኬ. . ." ሲቃ ያነቀው ድምፅ በስልኳ ውስጥ ሾልኮ መጣ። ". . . ሃሎ. . ምትክ"

ራሄል ልቧ ቡጭ ቡጭ ይል ጀመር። የተደወለው ካጤዳስ እንደሆነ ያወቀችው ምትኬ በሚለው ታላቅ ወንድሟ ሸዋንግዛው በሚጠራት ስም ስትጠራ ነው። "በዚህ ሰዓት ለምን ደወሉ?" ሳታስበው እጇን አንስታ ሰአት ተመለከተች። 1:37 ቀና ብላ ሰማዩን ተመለከተችው። የአዲስ አበባ ሰማይ ላይ ያሉ ከዋክብቶች ምድር ላይ ከተንቦገቦገው መብራት ፋክክር ሊጀምሩ ቦግ እልም ይላሉ። ጨረቃ አትታይም። ልቧን ደገፍ አርጋ መልስ ሰጠች።

"አቤት"

"ሸዋይርጋነኝ ካጤዳስ አላወእሽኝም"

"አአአአውቄዎታለሁ ምምምነነው ከመሽ?" ሳታስበው ምላሷ ተሳሰረባት። በድጋሚ እጇን ቀና አድርጋ ሰኣቷን ተመለከተች። 1:38

"አይ ሰላምስ ሰላም ነው። አንድ ነገር ላዋይሽ ፈለጌ ነበሪ" ድምፁ ውስጥ ሃዘን የሰማች ስለመሰላት ድምፁን ለመመርመር ሞከረች።

"ምንድነው ጋሼ? አባዬ ደህናም አይደል እንዴ?" ጆሮዋን አንቅታ ጠበቀች።

"እሱማ ደህና ነው ምን ይሆናል ብለሽ። እንደው ግን የትነሽ?" ድምፁ ውስጥ ሃዘን እንዳለ እርግጠኛ ሆነች። መንገድ ላይ ነኝ ብትለው ቤት ስትገቢ ነው የምነግርሽ እንደሚላት ገመተች። ራሷን ስትመረምር ቤት ድረስ የመታገስ አቅም እንደሌላት ተረዳችና ዋሸች።

"ቤት ነኝ"

"እስቲ ጥሪኝ" አለ እጁን ዘርግቶ። ወዲያው እያወራ ያለው በስልክ መሆኑን አስታውሶ እጁን ሰብስቦ ንግግሩን አረመ። "እስቲ እውነት በይኝ?"

"እእእእ. . . ንዴ አታምነኝም እንዴ!?" ውሸቷን ለመሸፈን እንደመቆጣት አደረጋት።

"በይ እቤት ከሆንሽ እትዬን አገናኚኝ"

"እሷ አሁን የለችም"

"በዚህ ሰኣት ወዴት ሄደው?" ድምፁ አንቺ ቀጣፊ እያላት ስለመሰላት ተሽማቀቀች።

"ቅዳስስ. . . እእእእ. . . እንትን. . .እእእእ. . . ሽንት ቤት ሻውር እየወሰደች ነው።" ተርበተበተች።

"ምን?"

"ገላዋን እየታጠበች ነው።" ቃሉን ጠበቅ አድርጋ ደገመችው።

"በይ ፈልጊያቸው ነውና ሲወጡ ጠብቀሽ አገናኚኝ እማወጋቸው አለ።"

"ለኔ አትነግረኝም? ማለቴ ምንድነው?"

"ቆይ ከሳቸው ጋር እናውጋና ነው አይ!" ስልኩ ተዘጋ።

ራሄል ልቧን ደገፍ ስታረገው ደረቷን ፈንቅሎ ሊወጣ ያሰበ ይመስል ይፍጨረጨራል። የሸዋይርጋ ድምፅ ሃዘን እንደገባው ተረድታለች። ቤት እስክትገባ ቸኩላ መኪናዋን አስነሳችና ነዳጅ መስጫውን በሃይል ተጫነችው።

ራሄል የግል ዶክተሯ ሰሞኑን ሙሉ ጤነኛ ስላልሆንሽ እረፍት ያስፈልግሻል ስላላት መሃል ፒያሳ ላይ ያለውን ወርቅ ቤትና ቦሌ አካባቢ ያለውን የምታስተዳድረውን ሆቴል ለማናጀሮቹ ለአስራ አምስት ቀን በስልክ እንጂ በአካል ስለማይገኛኙ አደራ ብላ የሚያስፈልገውን አሟልታ ነበር ወደ ቤት እየተመለሰች የነበረው።

ቤት ገብታ ሸዋይርጋንና እትዬ አሰገድን በስልክ አገናኝታ እሚባባሉትን ለመስማት አሰፍስፋ ቆማለች።

ወይዘሮ አሰገደች የሰሙት ዜና አስደንግጧቸው ሲርበተበቱ ራሄል ተደናግጣ "ምንድነው?" እያለች ትወተውታቸው ጀመር።

ስልኩን ከዘጉ በኃላ እንድትቀመጥ አድርገው የቆጨውን ሞት አረዷት። ራሄል ትገባበት ጉድጓድ ጠፍቷት እየተንሰቀሰቀች ካለቀሰች በኂላ አሁን ተነስቼ እሄዳለሁ አለች። ወይዘሮ አሰግድ በብዙ ልመና ጠዋት እንድትሄድ እሳቸውም እንደሚከተሏት ነግረው አረጋግተና ጣሰው የተባለው ሹፌራቸው ጋር ደውለው አስመጡት። አሰግድ እንዲቀሩ ቢወተውቱም አልቀርም ስላሉ ከሌሊቱ 10:00 ሲል ተነስተው ወደ መንዝ ገሰገሱ።

እትዬ አሰግድ ከራሄል ጀርባ ሆነው በስጋት እየተመለከቷት በግማሽ ልባቸው ሰውን ሰላም ይላሉ። እሳቸውም እንባቸውን መገደብ ተስኗቸው ያዝረበርቡታል።

ራሄል አባቷ ላይ ተጠምጥማ ናፍቆቷንም ሃዘኗንም እየገለፀች ታለቅስ ጀመር። ካባቷ ተላቃ ባይኗ ሸዋንግዛውን ብትፈልገው አጣችው።

ሸዋንግዛው ቄሶች ለፍታት እቤት ሲመጡ "የወንድሜን ገዳይ ሳልገል አላለቅስም፤ እኔ ሳልመጣ ወንድሜን እቀብራለሁ ብትሉ በቁሜ እንደቀበራችሁኝ እወቁ" ብሎ ደንፍቶ የወጣ እስካሁን አልተመለሰም። የሹሜ በበኩሏ ሸዋንግዛው የሄደበትን ስላላወቀች አጭር ምንሽሯን በግራ እጇ እንደያዘች ደጅ ደጁን ትንጎራደዳለች። መሰረት እምጥ ይግባ ስምጥ ጠፍቷል።

ራሄል የሹሜን ስታይ ተንደርድራ ሄዳ እያለቀሰች አቀፈቻት። የሹሜ ጉንጭ ላይ እንባ የለም። በግድ ስትናገርም ትንፋሽዋ እንደ እሳት ለበቅ ይጋረፋል። አይኗ ደም ለብሷል።

ሸዋንግዛው ደመኛውን ፍለጋ እንደቀተር እባብ እየተቅነዘነዘ መሃል ሜዳ ከተማ ሊገባ ትንሽ ሲቀረው ጠላቱ ማታ ቤቱን ሲያቃጥሉ በሩቁ ተመልክቶ መዘዜን ለሚስቴና ለልጆቼ አላተርፍም እነሱ ከሚገሉኝ ህግ እንዳረገ ያርገኝ" ብሎ እጁን እንደሰጠ ሰማ። ሸዋንግዛው በብሽቀት "እምለቀው መስሎት ነው!" ብሎ ዝቶ ወደ ፊቱ ገሰገሰ። መሃል ከተማ ሲገባ የያዘው መሳሪያ ፈቃድ እንደሌለውና ካልደበቀው ሊያሲዘው እንደሚችል ስላወቀ አንድ ወዳጁ ቤት ገብቶ ካሊም ተበደረና በካሊሙ ውስጥ አንጠለጠለው።

ሸዋንግዛው በካሊሙ ተሸፋፍኖ ተራ መንገደኛ መሰለና ወደ መሃል ሜዳ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ አመራ። ባካባቢው እንደደረሰ ወደ በሩ ሳይጠጋ ሁኔታውን መረመረ። ጣቢያውን ጠባቂ ፖሊሶች ቀልብ በማይስብ ሁኔታ ድንገት ችግር ቢፈጠርም ሊያመልጥበት የሚያስችለውን ቦታ መርጦ ሰው እንደሚጠብቅ ሆኖ ቆመ።

ብዙ ሳይቆይ የጣቢያው ባለሁለት ጋቢና መኪና ስትከንፍ መጥታ በሩ ጋር ቆመች። በሹፌሩ በኩልያለው በር ተከፈተ። በተከፈተው በር ተሸከርካሪ ኮልት የታጠቀ የደንብ ልብስ የለበሰ ሰው ወረደና የኂለኛውን በር ከፈተው። ወዲያው ተመሳሳይ የደንብ ልብስ የለበሰ ሰው ታጣፊ ክላሹን አስቀድሞ ዱብ ብሎ ወረደና ጣቱን መሳሪያው ምላጭ ላይ አሳርፎ አፈሙዙን ዘቅዝቆ ይጠብቅ ጀመር።

ሸዋንግዛው መሳሪያውን በካሊሙ እንደሸፈነው አወረደና አቀባበለው። ፖሊሱን ተከትሎ የወረደውን ሰው ሲያይ ተቅበተበጠ። ቀድሞ የወረደው ፖሊስ ስለጋረደው ለመተኮስ አልተመቸውም። ሁለቱ ፖሊሶች መሃል አድርገውት ወደጣቢያው ሊገቡ ሲሉ ፊት ለፊት ስለመጣለት አንድ አይኑን አጨንቁሮ አለሞ ተኮሰ። የሱን ተኩስ ተከትሎ ከመኪናው ኂላ ሌላ ጥይት ተተኩሶ ሊወድቅ የሚንገዳገደውን ጠላቱን መታው። ሸዋንግዛው ለሱ የተተኮሰ ጥይት ደመኛው ላይ ያረፈ መስሎት ራሱን ለመከላከል መሳሪያውን አመቻችቶ ወደ ላይ ሮጠ።

ፖሊሶቹ በሰላም የያዙት ወንጀለኛ ከመሃላቸው ሳል ከፊት ለፊታቸው በተተኮሰ ጥይት ተመቶ ሲወድቅ ደንግጠው ሊተኩሱ ሲዘጋጁ ሌላ ጥይት ከኂላቸው ስለተተኮሰ ግራ ገብቷቸው ወዴት እንደሚሄዱ ተደናግረው ቆሙ። ጣቢያው ውስጥ ያሉ ፖሊሶች በሙሉ ወጥተው ሁኔታውን ታዘቡና መሳሪያቸውን እያመቻቹ በያቅጣጫው ተበታተኑ።

ሸዋንግዛው ከፖሊስ ጣቢያ የገሰገሰ ምን ለብሼ ሲደርስ ከኂላው እየከነፈች የምትመጣ መኪና ተመልክቶ ቆም አለ። መኪናዋ አመጣጥ ስላላማረው ተራ መንገደኛ መስሎ ካሊሙን ተሸፋፍኖ ይጓዝ ጀመር። መኪናዋ አልፋው ስትሄድ ሩጫ አከል እርምጃ እየተራመደ ወደፊቱ ገሰገሰ። ዋናውን መንገድ ትቶ ወደግራው እንደታጠፈ ከኂላው አንድ ሰው እንደተከተለው አየና ሲዞር ከመሰረት ጋር ተገጣጠሙ።

መሰረትም ለማንም ሳይናገር የቆጨውን ገዳይ እገላለሁ ብሎ ወጥቶ ነበር። ፖሊስ ጣቢያው አካባቢ አድፍጦ መሳሪያውን እያመቻቸ ከኂላ ያለው ፖሊስ ከልሎት ቦታ ሲያማርጥ ድንገት የተተኮሰ ጥይት ኢላማውን ስለመታው ደንግጦ ሲተኩስ ጀርባው ላይ አሳረፈ። ቀድሞ ግንባሩን የተመታው ገዳይ ተጥመልምሎ ሲወድቅ ወደ ኂላው እግሬ አውጪኝ ፈረጠጠ።

ሸዋንግዛው እሱ ተኩሶ የጠላቱን ግንባር ከመታ በኂላ በድጋሚ የመታው ጥይት ከማ የተተኮሰ እንደሆነ ስላላወቀ ውስጥ ውስጡን ሲብሰለሰል ስለነበር ገና መሰረትን ሲያይ ማን እንደ ተኮሰ ገባው። ሳይነጋገሩ ተግባቡና መኪና በማይገባበት እያቆራረጡ ገሰገሱ። አጤዳስ ሲደርሱ ረግዶ ተይዞ ደረሱ።

አዳፋ ሸማ የለበሱ ሰዎች መስኩን ሞልተውታል። ርስበርስ ይነጋገራሉ፤ ያለቅሳሉ ይደጋገፋሉ. . . .

የሹሜ ገና መሰረትንና ሸዋንግዛውን ስታይ ወደነሱ ገሰገሰች። ሸዋንግዛው እንባው እየቀደመው አቀፋት። መሰረት ፈንጠር ብሎ ቆሞ እየየውን ያስነካው ጀመር። የሹሜ ባይነግሯትም ጣላቷ እንደሞተ ስታውቅ እንባ ወረዳት።

ሰው ደረቱን ጥሎ በየቦታው ያለቅሳል። ረግዶው መሃል የገባችው አስለቃሽ ግጥም እየደረደረች ማስለቀሷን ቀጠለች።

ወይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ሰው አፈር ነው ወይ!

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ድንጋዩም ይምጣለት ነጣፋ ነጣፋ

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ጭቃውም ይምጣለት በጭድ እየለፋ

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ቆጨው መከታችን ድራሹ እንዳይጠፋ

ስትል ሁሉም ደረታቸውን እየመቱ ዝልል ዝልል ይሉ ጀመር። ደረት ምቱ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# የግጥም ጥግ

## የፍቅር ቁልቁለት

የድሮ አፍቃሪ ቃል እየመረጠ
ከጥልቅ አይምሮው ሀረግ እያማጠ
የልብን ከልቡ... እየደጋገመ
እንደዚህ በማለት... ለአፍቃሪው ገጠመ
«ተነሽ ውዴ ሆይ! እንውጣ ወደላይ
እኔና አንች ብቻ እንብረር በሰማይ
ጭር ባለው ህዋ ምንም በሌለበት
በፍቅር ሀይቅ ላይ እንሳፈፍበት
እርቀን እንሄድ፡ ይርገብገብ ክንፋችን
ነፍሳት አይለፉ በመካከላችን
ዋሽንት ይነፋልን ይከረር ክራሩ
የመውደድ አማልክት ለእኛ ይዘምሩ
እንኑር ዘላለም በህይወት ልምላሜ
ሞት እስከሚረሳን አምላክ ሰጥቶን እድሜ»
ብሎ እንዳልገጠመ ብሎ እንዳልዘመረ
ዛሬ ላይ ሆነና እንዲህ ሲል ጀመረ
«ምነው ባላወቅኩሽ ባልገባሽ ከቤቴ
ይሻለኝ ነበረ ያው ብቸኝነቴ»
እያለ ያዜማል ብቻውን ተቀምጦ
በራስ ወዳድ መንፈስ እራሱን አላምጦ
ራሱን ሰልቅጦ።

## አሰሳ ሰው

ቀናት በከፋበት... ዘመን ባጠላበት
ችግር በበዛበት... ጭንቀት ባየለበት
መሰረት ተናውጦ... ሁኔታ ሲዛባ
የመፍትሄ ያለህ... ድምፅ ሲያስተጋባ
አንድ ባለ ራዕይ... አንድ መፍትሄ አፍላቂ
ለብዙዎች እፎታ ለብዙዎች በቂ
አለሁኝ የሚለን ጀግና አላየንም
አሰሰን... አሰሰን ሰው አላገኘንም።
ሰው የጠማችሁ ሰዎች
ሰው የራባችሁ ሰዎች
እስቲ እንደገና በተስፋ ተሞሉ
አብዝታችሁ ጓጉ
ሰው ባለበት ቦታ አንድ ሰው ፈልጉ።

ደስታ ተከስተ ባሕር ዳር ፀጥታ አገልግሎት

## <...ዘመን...>

ዘመን ነው አዚማም እንቅልፍ የደረበ፣
የሞት መርዝ ጭንብሉን የተከናነበ።
ፍጥረት የማይገፋው፣
ትውልድ የማያልፈው፣
የሞት ትጥቁን ታጥቆ ሁሌ ሚያንኮራፈው፣
ዘመን ነው እንቅልፋም ሞት የማያስከፋው።
ሞት የማይጠይቀው፤ የማያሳቅቀው።
ሰውማ ፈሪ ነው ሲተኛ ፀልዮ አመስጋኝ ሲነቃ፣
'ፉት ከጥንስሱ፤
'ፉት በትኩሱ፤ ሞትን በፌረቃ፣
ቀኑን እየተኛ ፈርቶ የሚነቃ።
ዘመን ነው እንቅልፋም ጊዜ ነው ዘልዛላ፣
ጎጆውን ቀልሶ በሞት አልባ ባላ፣
ትውልድ እየሸኘ የሚቀር ከኋላ።
የዓለምን ፍፃሜ የፈጣሪን ምፃት፣
ተኝቶ 'ሚጠብቅ ያላንዳች ፍርሃት።
ዘመን ነው ዘልዛላ ጊዜ ነው ጎታታ፣
ትውልድ ሲንደረደር፤
ቅልጥም የሚሰብር፤ ጉልበት የሚመታ፣
ትውልዱ ቀና ሲል አንገት የሚቀላ፣
በእንብርክክ የሚያስኬድ፤ ጉልበቱ እስኪተላ።
ዘመን ነው አለቃ የዚህ አለም ቁንጮ፣
ተኝቶ እማይነቃ ፍጥረታት ሲንጫጩ።

[ጥቅምት14/2009ዓ.ም] ባህር-ዳር

ያንተአምላክ ተመስገን (አካውንቲንግና ፋይናንስ ት/ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ)

## እሳትን በውሃ

ጥርሱን እንጂ ሆዱን
መቼ ታውቀውና
ሲሸጥህ ሲታገል
የኔን ያልከውማ
በንዴት ሲጠፋህ
የሞታደርገው
መቼ ያን ጥርሱን
በሀይል አታርግፈው
አይተህ እንዳላየህ
ሆነህ ብታልፈው
ምንም ሳይሰማህ
ነገሩን አቅልለህ
ብትመለከተው
ይህ ነው ብልህነት
ማሸነፍ ለፍቅር
በማይሸነፈው

ነፃነት መሰረት ከባሕል ማዕከል

## ፍናፍንት ...

ከገጽ 11 የዞረ

ጋር ተዳምሮ ሲሰማ ልብ ያንቦጫ ቡጫል፤ ሳይወዱ አልቅሱ አልቅሱ ያስብላል።

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

እባክን ገናገፑ አርግለት ቀዳዳ

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ጥቃት ቢመጣብን መሸሎኪያ እንዳያጣ

ዋይ ዋይ - ዋይ ዋይ

ህዝቡ ተሰብስቦ አስክሬን አነሱና ወደ ባለወልድ ቤተክረስቲያን አመሩ። ደረት ተጥሎ፣ ነጠላ ተዘቅዝቆ እያለቀሱ መለስ ከማለታቸው በርካታ ፖሊሶች ወደነሱ ሲመጡ ተመለከቱ።

መሰረትና ሸዋንግዛው መሳሪያቸውን አውርደው በጃቸው ያዙ። የሹሜ ወደ ፊት ብቅ አለች። ራሄል ከወንድሟ ጎን ቆማ በድንጋጤ ትርበተበት ጀመር።

ይቀጥላል....

# About Chinese Tests - HSK Exam

**Dr. Zhang Wenxia**

**(continued from November publlication)**

## BCT: Business Chinese Test

To meet Chinese language learners' need for a business Chinese test, the Confucius Institute Headquarters (Hanban) commissioned the International Business Chinese Language Teaching and Resource Development Base, University of International Business and Economics to organize Chinese and overseas experts on business Chinese language teaching, linguistics, psychology and educational measurement to revise the Business Chinese Test (BCT) which has existed since 2006 on the basis of the latest research results on international language testing and business Chinese from recent years.

The new BCT, as an international,standardized test of Chinese language proficiency, focuses on assessing non-native Chinese speakers' abilities to use the Chinese language in real business or common working environments and evaluating the language tasks they are able to complete. It aims to provide references for companies to recruit and select employees, for schools and training institutions to organize teaching activities, and for learners to evaluate themselves.

The BCT, as a test series, consists of three independent tests: BCT (A), BCT (B) and the BCT Speaking Test. The BCT (A), which is oriented towards beginners, is designed to examine test takers' ability to communicate in Chinese in daily life and during basic business activities. The BCT (B),which is oriented towards intermediate and advanced learners, is designed to examine test takers' ability to communicate in Chinese during complex business activities. The BCT Speaking Test, which is oriented towards learners of all levels, adopts the form of a computer-based test as well as personalized and targeted questions to examine test takers' ability to complete various communicative tasks by using spoken Chinese.

The BCT has the following characteristics: first, it focuses on the practical use of Chinese when conducting business activities. The test, following the principle of practicality, oriented towards speaking and listening, and emphasizing abilities in the workplace, aims to recreate actual situations in the workplace. Second, it has set the Standards for Business Chinese Language Competence and advocates a combination of teaching and examination as a method of improving Chinese language skills. The Standards for Business Chinese Language Competence, which is based on large-scale surveys and data analyses and aligned with the BCT Outlines, provides a basis for a refined assessment of competence and systematic teaching activities. Third, it includes business culture as a part of the test so as to improve learners' intercultural communicative competence.

### Test Takers

The BCT is held for non-native Chinese speakers. Anyone who is a non-native speaker, whether capable of basic communication or fairly skillful communication in Chinese, may take the BCT. There are no restrictions on test takers' age, education or length of time spent learning Chinese.

### Test Time and Location

The BCT is held regularly in mainland China and other countries each year. In addition, BCT can provide special testing services as required by relevant enterprises or organizations.

For information about the test dates and test centers for the BCT, please log on to the Chinese test service website www.chinesetest.cn.

### Test Purposes

1.Provide a basis for employers to assess non-native Chinese speakers' (candidates) Chinese competence in daily work. Test scores can be used as a reference for employee recruitment, selection, placement and promotion.

2.Help relevant teaching and training institutions to assess students' business Chinese proficiency in recruitment, class divisions, and granting credits.

3.Help learners to improve and evaluate their business Chinese competence.

### BCT (A)

The BCT (A) is an international, standardized exam in Chinese language proficiency that focuses on testing non-native Chinese speakers' abilities to use the Chinese language in real business or common working environments, and that evaluates the language tasks they are able to complete. Following the principle of practicality, oriented towards speaking and listening, and emphasizing abilities in the workplace, this test aims to recreate actual situations in the workplace and takes practical content for communications as the method of examining test takers' abilities to use Chinese to meet their needs in a working environment.

### I. Test Structure

BCT (A) contains 70 question sand consists of three parts: listening, reading and writing.

| Test Item | | Number of Questions | | Duration of Test (minutes) |
|---|---|---|---|---|
| 1. Listening | Section One | 10 | 30 | About 20 |
| | Section Two | 10 | | |
| | Section Three | 10 | | |
| 2. Reading | Section One | 10 | 30 | 30 |
| | Section Two | 20 | | |
| 3. Writing | | 10 | | 10 |
| Mark your answers on the Answer Sheet (after the listening section) | | | | 5 |
| Total | / | 30 | 70 | About 65 |

Table 1 Test Structure of BCT (A)

#### 1. Listening

Section One contains ten questions. You will hear a word or phrase for each question twice. On the test paper, there is a picture for each question. Answer whether the content of the picture is true or false according to what you hear.

Section Two contains ten questions. You will hear a sentence for each question twice. On the test paper, there are three pictures for each question. Choose the right one according to what you hear.

Section Three contains ten questions. For each question, you will hear a dialogue between two people and a question based on the dialogue twice. Choose the best answer from the three choices on the test paper according to what you hear.

#### 2. Reading

Section One contains ten questions. One or two sentences with a blank will be provided for each of the first five questions. Choose the best answer from the choices to complete the sentence. The other five questions are five blanks in a table or a short passage of practical writing. Choose the best answers to complete the table or the passage.

Section Two contains twenty questions. A series of reading materials will be provided, including pictures, tables, paragraphs, passages, etc. Each piece of reading material will be followed by one to three questions, with three choices. Choose the best answer to the question.

#### 3. Writing

This part contains ten questions. For each question, there is a sentence with a blank. Use the correct Chinese character or phrase (Pinyin of the word or phrase will be provided) to fill in the blank.

### II. Reference Vocabulary

The BCT (A) has set up a reference vocabulary of 600 words according to language competence, can-do statements, word frequencies of various authoritative Chinese corpora, and the actual state of international Chinese language teaching.

### III. Score System

The BCT (A) score report records a test taker's sub-test scores and total score, without setting a passing score. The report will also provide competence descriptions for all levels of test takers.

The BCT (A) test paper consists of three sub-tests: listening, reading and writing, with a total score of 300 points. Its score system is shown in the table below:

| | Listening | Reading | Writing | Total |
|---|---|---|---|---|
| No. of questions | 30 | 30 | 10 | 70 |
| Maximum score of sub-test | 100 | 100 | 100 | 300 |

Table 3 Score System of BCT (A)

### IV. Test Principles

Promote learning through examination: encourage Chinese language learners' interest and confidence, and further broaden the scope of the test in accordance with the actual demands of overseas Business Chinese learners and Chinese speakers in a general working environment.

Promote teaching through examination: provide teachers and self-learners with graded, task-based teaching resource sand suggestions related to business Chinese, and help teaching and training institutions systematically and effectively improve business Chinese learners and speakers' abilities to use the Chinese language in real business or common working environments.

Provide positive feedback for test takers: evaluate test takers' ability to complete various language tasks by asking them to carry out a series of typical business language tasks and provide positive feedback for Chinese language learners to plan their future studies.

### BCT (B)

The BCT (B) is an international, standardized exam in Chinese language proficiency that focuses on testing non-native Chinese speakers' abilities to use the Chinese language in real business or common working environments, and that evaluates the language tasks they are able to complete. Following the principle of practicality, oriented towards speaking and listening, and emphasizing abilities in the workplace, this test aims to recreate actual situations in the workplace and takes practical content for

continued on page 14

# About Chinese Tests

continued from page 13

communications as the method of examining test takers' abilities to use Chinese to meet their needs in the working environment.

### I. Test Structure

The BCT (B) written test contains 92 question sand consists of three parts: listening, reading and writing.

| Test Item | | Number of Questions | | Duration of Test (minutes) |
|---|---|---|---|---|
| Write down personal information (before the listening section starts) | | | | 5 |
| 1. Listening | Section One | 20 | 50 | About 40 |
| | Section Two | 15 | | |
| | Section Three | 15 | | |
| 2. Reading | Section One | 20 | 40 | 60 |
| | Section Two | 10 | | |
| | Section Three | 10 | | |
| 3. Writing | | 2 | | 10 |
| Mark your answers on the Answer Sheet (after the listening section) | | | | 5 |
| Total | / | 92 | | About 150 |

Table 1 Structure of BCT (B) Written Test

The duration of the whole test is about 150 minutes (including 5 minutes for writing down personal information).

#### 1. Listening

Section One contains twenty questions. A two-sentence dialogue between two people and a question based on the dialogue will be read once for each question. Choose the best answer from the four choices on the test paper according to what you hear.

Section Two contains fifteen questions. A four-sentence dialogue between two people and a question based on the dialogue will be read once for each question. Choose the best answer from the four choices on the test paper according to what you hear.

Section Three contains fifteen questions. Five passages followed bya few questions will be read to you once. Choose the best answer from the choices on the test paper according to what you hear.

#### 2. Reading

Section One contains twenty questions. A series of reading materials will be provided, including pictures, tables, paragraphs, passages, etc. Each piece of reading material will be followed by a few questions, each with four choices. Choose the best answer to the question.

Section Two contains ten questions. There are two passages with five blanks each. Choose five best answers from seven choices to complete each passage according to the context.

Section Three contains ten questions. This section is divided into two groups, each with five questions. Four passages and several questions or sentences will be provided on the test paper. Match each question or sentence with its related passage.

#### 3. Writing

Section One contains one question. A written text or table will be provided. Write at least 80 Chinese characters according to the directions.

Section Two contains one question. A written text or table will be provided. Write at least 150 Chinese characters according to the directions.

### II. Reference Vocabulary

The BCT (B) has set up a reference vocabulary of 4000 words according to language competence, can-do statements, word frequencies of various authoritative Chinese corpora, and the state of international Chinese language teaching.

### III. Score System

The BCT (B) score report records a test taker's sub-test scores and total score, without setting any passing score. The report will also provide competence descriptions for all levels of test takers. The BCT (B) written test consists of three sub-tests: listening, reading and writing, with a total score of 300 points. Its score system is shown in the table below:

| | Listening | Reading | Writing | Total |
|---|---|---|---|---|
| Number of questions | 50 | 40 | 2 | 92 |
| Maximum score of sub-test | 100 | 100 | 100 | 300 |

Table 3 Score System of BCT (B)

### IV. Test Principles

Promote learning through examination: encourage Chinese language learners' interest and confidence, and further broaden the scope of the test in accordance with the actual demands of overseas Business Chinese learners and Chinese speakers in a general working environment.

Promote teaching through examination: provide teachers and self-learners with graded, task-based teaching resource sand suggestions related to business Chinese, and help teaching and training institutions systematically and effectively improve business Chinese learners and speakers' Chinese language communicative competence in a realistic business environment.

Provide positive feedback: evaluate test takers' ability to complete various language tasks in a business environment by asking them to carry out a series of typical business language tasks and provide positive feedback for Chinese language learners to plan their future studies.

# ለአዳዲስ ወላጆች /እናቶች/

ከገጽ 5 የዞረ

4ኛ. አዲስ የተወለደ ልጅዎ የአጠባብ ስርዓቱ /ሂደቱ/ ሊለያይ እንደሚችል ይወቁ፡-

አዲስ የተወለደ ልጅዎ በየቀኑ የግድ አንድ አይነት መጠን ያለው የጡት አጠባብ ላይኖረዉ ይችላል፡፡ እድገቱ በፍጥነት በሚሆን ወቅት ለምሳሌ ከተወለደ በ2ኛና በ3ኛው ሳምንት እንዲሁም 6ኛ ሳምንቱ አካባቢ በአንድ ጊዜ ብዙ ሊጠባና እንዲሁም ቶሎ ቶሎ ሊርበዉ ስለሚችል ከላይ የተጠቀሰዉን የሰዓት ገደብ (በቀን 8-12 ጊዜ) ሳይጠብቁ በቶሎ የልጅዎን የረሃብ ስሜት ምልክቶች በመረዳት ማጥባት ያስፈልጋል፡፡

5ኛ. ዉስጥዎን /ደመነፍስዎንና ልጅዎን ይመኑ፡-

ልጅዎ በቂዉን ያህል አልጠባም ብለው ሊጨነቁ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ልጅዎ ምን ያህል እንደሚያስፈልገዉ እራሱ ያዉቃል፡፡ ልጁ ምን ያህልና በምን ያህል ልዩነት ጠባ ላይ ሳይሆን በሚከተሉት ነገሮች ላይ በይበልጥ ትኩረት ያድርጉ፡-

- ቋሚ /ተከታታይነት ያለዉ ክብደት መጨመሩን፣
- በጡት አጠባቡ መካከል እርካታ /ምቾት መኖሩን፣

ልጅዎ ክብደት እየጨመረ የማይመጣ ከሆነና ጡት የመጥባት ፍላጎት ከሌለዉ፣ የጤና ባለሙያዎን ያማክሩ፡፡

6ኛ.እያንዳንዱን የጡት ማጥቢያ ጊዜ ከልጅዎ ጋር የጠበቀ ግንኙነት /ትስስር (Bond)/የሚፈጥሩበት ጊዜ አድርገው ይውሰዱት፡-

ጡት በሚያጠቡበት ወቅት ልጅዎን ወደ ሰዉነትዎ አስጠግቶ መያዝ፤ የልጅዎን አይን አይኑን ማየት፤ በቀስታ ከልጅዎ ጋር መጫወት እንዲሁም እያንዳንዱን የጡት መጥቢያ ወቅት የልጅዎን የደህንነት ስሜት (sense of security)፣ አመኔታ (trust) እና ምቾት እንዲሰማዉ ለማጎልበት አጋጣሚዉን ይፈጥርልዎታል፡፡

7ኛ. እርዳታ መቼ እንደሚያስፈልግዎ ይወቁ /ይረዱ/፡-

ለምሳሌ ጡት በማጥባት ወቅት ችግር ካገጠመዎት፤ ጡት በሚያጠቡበት ወቅት ህመም ካለዎት ወይም ልጅዎ ክብደት የማይጨምር ከሆነ የጤና ባለሙያዎን ያማክሩ፡፡

# The 70:30 Policy Dilemma

continued from page 10

engaged in more efficient use of existing resources, strategic planning for new resource acquisition and organizational changes that provide greater autonomy. That is how prestigious universities such as Harvard, Yale, MIT have been immune to this challenge and laid the legacy of excellence in research and innovation.

In a nutshell, the pressures to raise the educational quality of universities for all students may require new ways of providing learning opportunities including the use of innovative instructional approaches, better use of technology, internships, access to ICT facilities, and so on. However, in a rapidly expanding system, quality and relevance will also fall unless effective strategies are implemented to maintain standards.

***Personal Prologue***

***Some might argue that I hold pessimistic view towards the 70:30 policy for showing the challenges since I am from the 'soft', social science; but the fact is I am rather cautiously optimistic in clearing the way forward and indicating the challenges, locating the alternatives. In this regard, I might be opinionated to some extent, but the fact on the ground appears to be not far from my reflective opinion. Hence, I am happy to discuss, share views and accept any comments regarding my brief reflection on the policy and the prospects of maintaining it. Thanks.***

# THE UNTOLD STORIES ...

continued from page 7

Some of you might question me why these kinds of massive intellectual contributions that have been provided by the staff of the university have gone unreported. I personally believe that it may be partly because the university might have been negligent in not reporting about the services, or it might because the staffs of the college were not interested in reporting what has been done.

So far, having highlighted the duty and responsibility of health professionals, I have pinpointed their invaluable contribution to the public by taking the college of health sciences at BDU as an example. Next, I shall discuss on the wider implications of these insightful values for the college of medicine and health sciences. Well, to avoid confusions on which comes first; teacher or clinician? , and decide on what to do next, we need to understand the dynamic of health professionals, which we are born as a physician first and as a teacher second. My question, here, is that why some health professionals as university teachers in various state universities have abandoned their professional obligation with the pathetic excuse for teaching?

To put this in simpler terms, the duty of state universities is to promote the academic mission of the country. However, it is vital to stress that for the full realization of the uniqueness of the profession of health, every health professional must be committed to show great compassion individually or in a team in saving lives. In support, in an attempt to sort out the management paradox three years ago, both ministry of education and ministry of health have disclosed that all the 28 medical schools in the country except one have difficulty in achieving their primary objective (teaching through service delivery) because in each state university, the administration was 'system ignorant' in managing health professionals and hospitals. Accordingly, this has lead to the initiative of developing the University Hospital Management Guideline. The main objective of the guideline is to help university administrations to exercise the power given by Higher Education Proclamation No. 650/2009 and Council of Ministers Regulations No. 210/2011.This proclamation gives not only clear ideas for university administration to deal with their financial and administrative systems adaptable to the requirements of the core activities of institutions of higher education, but also to determine, in broad terms, the organizational structures and the powers and duties of the major units of the institutions.

As a result, health Science Colleges in most universities are now adopting the guideline and changing the management. Bahir Dar University is struggling to do so. Needless to say, the changing environment and contemporary global view of health care requires designing better systems to address organizational flows and patient care. Likewise, this aim can be attained through changes in the management and academic culture of health science colleges and teaching hospitals focusing on quality of care, patient safety under updated clinical protocols, and modern research methods. BDU as a huge institution can strive for its mission but the administration also needs to create favorable working management to the broad mission of the health science college.

Generally, diffusion of ideas and their practical implementations may take time partly because they often require people to change the way they have lived as the guideline for health sciences changing management met resistance to take the initiative forward. However, if we are committed to see what we are envisioned for 2020, let us go to the inevitable of change management. Indeed, apart from producing competent, knowledgeable and skilled human power, the college is dedicated to promote innovation and excellence in patient care, teaching, research and service to the communities.

...the changing environment and contemporary global view of health care requires designing better systems to address organizational flows and patient care.

# :: እና ¡

በታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)
(www.facebook.com/ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ)
የ፫ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ

ስምን መላክ ያወጣዋል፡፡" ይላል ያገሬ ሰው፡፡ መንገደ ሰማይ በሚለው ሃማኖታዊ መፀሃፍ ላይ እንደተፃፈው እኔም እንዳነበብኩት ደግሞ መልአክ በሁለት ይከፈላል፡፡ መልአከ ብርሃንና መልአከ ፅልመት ተብሎ፡፡ ስለዚህ ስምን መልአክ ያወጣዋል ሲባል መልአከ ብርሃን ስም ያወጣል፤ መልአከ ፅልመትም ስም ያወጣል ማለት ነው፡፡

መልአኮቹ ስም ሲያወጡ ይለያያሉ፡፡ ልዩነታቸው ደግሞ አወጣጥ ላይ ነው እንጂ ስም ላይ አይደለም፡፡ ማለቴ መላከብርሃን ይሄ የኔ ስም ነው ያለው ስም የለም፤ መላከ ፀልመትም ይሄ ይሄ የኔ ስም ነው ያለው የለም፡፡ መሰረታዊ አወጣጥ ልዩነታቸው ድምፀት ነው፡፡ መልአከ ፅልመት ስም ሲያወጣ መጨረሻ ላይ ትእምርተ ስላቅ ያስቀምጣል፡፡ መልአከ ብርሃን ደግሞ አራት ነጥብ፡፡ በቃ! መሰረታዊ ልዩነቱ ይሄው ነው፡፡ (የምትጨምሩት ካለ ይፈቀዳል)

ለምሳሌ መልአከ ፅልመት አንድ ጨቅላ ገና ከነ ቃጭሉ ዱብ ሲል ተስገብግቦ "ወንድይፍራው" ይለዋል፡፡ መጨረሻ ላይ ስላቅ አስቀምጦ፡፡ በአራሲቱ ዙሪያ የተሰበሰቡት ሁሉ ይሁን ይሁን ተባብለው የስም ማፅደቂያ ዳቧቸውን እየቀለፈዱ ገንፎ ይጠብቃሉ፡፡ "ወንዲፍራው" አድጎ ምን ይሆናል? ፈሪ፣ ቦቅቧቃ፣ ጦርጧራ፣ በጭባጫ - የወንድ አልጫ . . .

መላከ ብርሃንም ይህን ስም ያወጣል፡፡ ከስሙ ኋላ ደግሞ አራት ነጥን ያስቀምጣል፡፡ ወንዲፍራው አድጎ ምን ይሆናል፡፡ አገር አስከባሪ፣ ደፋር፣ በሁሉ የተከበረ ወየተፈራ፡፡

አንዲቷ ደሞ ስትመጣ እትብቷ እንኳ ሳይቆረጥ ፅልሜ ይደርስና ስም አውጪዎች ላይ ይሰፍራል፡፡ ጉብ! ከነ ሙሉ ግርማ ሞገሱ፡፡ ቁጥጥጥጥ ከላይ ወጥቶ. . . መቼም ለሱ ማረፊያ ቅርብ ነን፡፡

ስም ሲወጣ "የውብ ዳር"" ይላል፡፡ የውብዳር ስታድግ ምን ትሆናለች የውብ ዳር፡፡ በቃ፡፡ ጥያቄው የሚነሳው የውብ ዳር የምትሰለፍበት የውበት ዳር ከየትኛው በኩል ያለው ነው የሚለው ነው፡፡ መልሱ ከመጨረሻ የሚለው ይሆናል፡፡ ከሁሉ ቀፋፊዎች ቀድማ፡፡ ከሷ ቀጥሎ ሄዶ ሄዶ ሄዶ. ... እልፍ ፉንጋዎችን አልፎ የውበት መስመር ይጀምራል፡፡ የውበት መስመር ዳዳዳዳዳዳር ላይ ሌላዋ "የውብ ዳር" ትገኛለች፡፡ ስሟን ብሬ ያውጣላት፡፡ ከስሟ በኋላ ስላቅ ሳይሆን አራት ነጥብ የተቀመጠላት፡፡

እናንተ ካልቀጠላችሁ እኔ ጨርሻለሁ!



# Photo Gallery

## Consultative workshop on Integrating Construction Industry Stakeholders organized by Bahir Dar Institue of Technology, Faculty of Civil and Water resources Engineering



















### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን የተለያዩ ጹህፎች፣ ማህበራዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች፣ የካርቱን ስዕሎች፣ ቀልድ፣ ግጥም እና የመሳሰሉትን ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 512 ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com በመላክ መሳተፍ ይችላሉ፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ